# የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ የ2008 የስራ ዘመን የዘጠኝ ወራት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት

**ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ**
**ሚያዝያ 2008**
**ዓዲግራት**

## መውጫ


| | ይዘት | ገፅ |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ | 2 |
| 2 | መሰረታዊ አሃዛዊ መረጃዎች | 3 |
| | 2.1. ተማሪዎች የሚመለከት | 3 |
| | 2.2. መምህራንና የአካዳሚክ ቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች | 13 |
| | 2.3. ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች | 16 |
| 3 | ለ2008 የተፈቀደልን ባጀትና አጠቃቀሙ | 18 |
| | 3.1. መደበኛ በጀት | 18 |
| | 3.2. ካፒታል በጀት | 19 |
| 4 | የግንባታ ስራዎች አፈፃፀም | 21 |
| 5 | የእቅድ አፈፃፀም | 24 |
| | 5.1. የቁልፍ ተግባር አፈፃፀም | 24 |
| | 5.2. የዝግጅት ስልጠናዎች | 26 |
| | 5.3. የትምህርት አሰጣጥ | 28 |
| | 5.4. ምርምርና ህብረተሰብ አገልግሎት | 29 |
| | 5.5. ለሴት ተማሪዎች የተደረገ ድጋፍ | 30 |
| | 5.6. ደረጃውን የጠበቀ የዳታ ሰንተርና የካምፓስ ኔትወርክ ዝርጋታ | 31 |
| | 5.7. የ2008 የስራ ዘመን የዘጠኝ ወራት የስራ አፈፃፀም ሰንጠረዥ | 34 |
| 6 | ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች | 54 |

## 1. መግቢያ

ከዘጠኝ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ሆኖ ሲቋቋም ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ በአምስት አመታት ውስጥ 15ሺ ያህል መደበኛ ተማሪዎችን ሊያስተናግድ ይችላል የሚል እቅድ ተይዞለት ነው። ዩኒቨርሲቲው እነሆ በ2008 አምስተኛ ዙር መደበኛ ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተናገድ ላይ ይገኛል። ዩኒቨርሲቲው መደበኛ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎችን በመቀበል ስራውን የጀመረው ህዳር 26/2004 ሲሆን ያኔ 960 ተማሪዎችን በአራት ኮሌጆችና በአስራ ሶስት ትምህርት ክፍሎች ተቀብሎ ነበር። ከመደበኛው ትምህርት ጎን ለጎን የማታ ተከታታይ ትምህርት በ2004 ሁለተኛ ሰሚስተር፤ የክረምት ተከታታይ ትምህርት ደግሞ በ2005 ክረምት በመጀመር ዩኒቨርሲቲው በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ተማሪዎችን ማስተናገድ ችሏል። ለንፅፅር ይረዳ ዘንድ በ2007 የነበሩት ተማሪዎች ብዛት ካሳየን በኋላ በ2008 ያሉን ተማሪዎች ብዛት ደግሞ ቀጥለን እናስቀምጣለን። በ2007 የትምህርት አመት ዩኒቨርሲቲው የነበሩት ተማሪዎች ብዛት የሚከተለውን ይመስል ነበር (የክረምት ተከታታይ በ2006 ክረምት ላይ የነበሩ ተማሪዎችን የሚያሳይ ሆኖ ሌሎች ግን በ2007 ሁለተኛ ሰሚስተር የነበሩት የተማሪዎች ብዛይ የሚያመለክት ነው)፤

- መደበኛ ቅድመ ምረቃ ተማሪዎች፤ 10027 (5875 ወንድ እና 4152 ሴት)
- መደበኛ ድህረ ምረቃ ተማሪዎች፤ 13 (12 ወንድ እና 1 ሴት)
- የማታ ተከታታይ ቅድመ ምረቃ፤ 923 (524 ወንድ እና 399 ሴት)
- የማታ ተከታታይ ድህረ ምረቃ፤ 95 (87 ወንድ እና 8 ሴት)
- የክረምት ተከታታይ፤ 2320 (1757 ወንድ እና 563 ሴት)
- ጠቅላላ ድምር፤ 13378 (8255 ወንድ እና 5123 ሴት)

ዩኒቨርሲቲው በ2008 ሁለተኛ ሰሚስተር ያሉት የተማሪዎች ብዛት ዝቅ ብሎ የተመለከተውን ይመስላል። የክረምት ተከታታይ ተማሪዎች በ2007 ክረምት ላይ ተመዝግበው ትምህርት ላይ የነበሩትን የሚያመለክት ሆኖ ሌሎቹ ግን በ2008 ሁለተኛ ሰሚስተር ላይ ተመዝግበው በመማር ላይ ያሉትን የሚያሳይ ነው። በዚሁም መሰረት ዩኒቨርሰቲው በ2008 የትምህርት ዘመን በሁለተኛው ሰሚስተር ያሉት ተማሪዎች ብዛት 18038 የደረሰ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

- መደበኛ ቅድመ ምረቃ ተማሪዎች፤ 12696 (7547 ወንድ እና 5149 ሴት)
- መደበኛ ድህረ ምረቃ ተማሪዎች፤ 53 (46 ወንድ እና 7 ሴት)
- የማታ ተከታታይ ቅድመ ምረቃ፤ 1177 (691 ወንድ እና 486 ሴት)
- የማታ ተከታታይ ድህረ ምረቃ፤ 150 (135 ወንድ እና 15 ሴት)
- የክረምት ተከታታይ (2007 ክረምት)፤ 3962 (2837 ወንድ እና 1125 ሴት)
- ጠቅላላ ድምር፤ 18038 (11256 ወንድ እና 6782 ሴት)

የፕሮግራሞችን ብዛት በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው በ2008 በመደበኛው እና በማታ ተከታታይ መርሃ ግብሮች 40 የቅድመ ምረቃ እና 6 የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች በማካሄድ ላይ ይገኛል። በ2007 የነበሩት የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ብዛት 2 (ማለትም Master of Accounting and Finance, and Master of Business Administration) ሲሆን በ2008 አራት አዳዲስ የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች (ማለትም MSc in Computer Science, MSc in Information Technology, MSc in Animal Production and Technology, and MA in Sociology) ተከፍተው ተማሪዎች በመደበኛው እና በተከታታይ መርሃ ግብር ተመዝግበው በመማር ላይ ይገኛሉ።

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ እንደሌሎች የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ሶስት ዋና ዋና ተልእኮዎች ያሉት ሲሆን እነሱም፤ ማስተማር፤ ምርምር እና የህብረተሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማከናወን ናቸው። ዩኒቨርሲቲያችን እነዚህን ተልእኮዎች በአጥጋቢ መልኩ ለማሳካት ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ የ2008 ዓመታዊ እቅዱን ካዘጋጀ በኋላ ከዝግጅት ምእራፍ

ወደ ትግበራ ምእራፍ ተሸጋግሮ በኣመቱ ዘጠኝ ወራት ውስጥ ያከናወናቸው ስራዎች እነሆ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 2. መሰረታዊ አሃዛዊ መረጃዎች

### 2.1 ተማሪዎችን የሚመለከት

ዩኒቨርሲቲው በ2004 ስራ ሲጀምር የተመደቡለት መደበኛ ተማረዎች ብዛት 960 የነበረ ሲሆን በ2005 ደግሞ 3141 አዲስ ተማሪዎች በመደበኛነት እና 117 ኤርትራውያን ስደተኞች በድምሩ 3258 ተማሪዎች በስድስት ኮሌጆች እና በ26 የትምህርት ፕሮግራሞች ተመድበውለት ነበር። በ2006 የተመደቡት አዲስ ተማሪዎች በመደበኛነት 4289 እና የኤርትራ ስደተኞች 130 በድምሩ 4419 ተማሪዎች ነበሩ። በ2007 የተመደቡት ተማሪዎች በመደበኛነት 4289 እና የኤርትራ ስደተኞች 130 በድምሩ 4419 ተማሪዎች ነበሩ። በተመሳሳይ መልኩ በ2008 የተመደቡልን ኣዲስ ተማሪዎች ብዛት 5244 ሆኖ ከዚህም በተጨማሪ 45 ኤርትራውያንና 32 ሶማልያውያን በድምሩ 5321 ተማሪዎች ተመድበውልናል።

በ2007 የትምህርት ዘመን መጨረሻ ኣከባቢ ለ2008 የትምህርት ኣመት መቀበል የምንችለውን የኣዲስ ተማሪዎች ብዛት እንድናሳውቅ በቀረበልን ጥያቄ መሰረት ለ2008 ይደርሱልናል ብለን ያሰብናቸውን የህንፃዎች፣ የመሰረተ ልማት እና የሰው ሃይል ኣቅማችንን መሰረት በማድረግ ኣምስት ሺ ያህል ኣዲስ ተማሪዎችን መቀበል እንደምንችል ያሳወቅን ቢሆንም በኣመቱ ወደ ዩኒቨርሲቲዎች ሊመደቡ የተዘጋጁ ተማሪዎች ብዛት ከፍተኛነት ግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ ኣምስት መቶ ተማሪዎችን እንድንቀበል በትምህርት ሚኒስቴር በቀረበልን ጥያቄ መሰረት 5500 ኣዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል ዝግጅቶች ኣድርገን ስለነበረ የተመደቡልን 5321 ተማሪዎች ከጠበቅነው ቁጥር በላይ ኣልነበረም። ከኤርትራና ከሶማልያ የተመደቡልን ተማሪዎችን ሳይጨምር ከትምህርት ሚኒስቴር በቀጥታ የተመደቡልና ኣዲስ ተማሪዎች 5244 ሲሆን ከዚህም ውስጥ 2150 (ማለትም 41%) ሴቶች ሲሆኑ የተቀሩት 3094 (ማለትም 59%) ወንዶች ናቸው። የመጡበትን ክልል እና ያገኙት የዩኒቨርሰቲ መግቢያ ነጥብ በተመለከተ ደግሞ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ 1፤ ኣዲስ የተመደቡ ተማሪዎች በመጡበት ክልል

| ክልል (ከተማ) | ብዛት | መቶኛ |
|---|---:|---:|
| ትግራይ | 2460 | 46.91 |
| ኣማራ | 1265 | 24.12 |
| ደቡብ ህዝቦች | 506 | 9.65 |
| ኣዲስ አበባ | 373 | 7.11 |
| ኦሮሚያ | 263 | 5.02 |
| ሶማሌ | 183 | 3.49 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 67 | 1.28 |
| ዓፋር | 51 | 0.97 |
| ጋምቤላ | 43 | 0.82 |
| ድሬዳዋ | 19 | 0.36 |
| ሃረሪ | 6 | 0.11 |
| ሌሎች (ሪያድ እና ጂዳ) | 8 | 0.15 |
| | 5244 | 100.00 |

ከላይ እንደሚታየው ወደ ዩኒቨርሲቲው ከተመደቡት ኣዲስ ተማሪዎች ውስጥ 47% የሚሆኑት ከትግራይ ክልል ሲሆን የተቀሩት 53% የሚሆኑት ደግሞ ከሌሎች ክልሎች የተመደቡ ናቸው። ከትግራይ ክልል ቀጥሎ በርካታ ተማሪዎች (24%) የተመደቡት ከኣማራ ክልል ሲሆን ከዚሁ ቀጥሎ ደግሞ ወደ 10% ያህል የሚሆኑት ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የተመደቡ ናቸው።

የተመደቡት ኣዲስ ተማሪዎች ባስመዘገቡት የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ነጥብ ሲታይ ደግሞ በሚከተለው ሰንጠረዥ የተጠቃለለውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 2፤ የተመደቡት ኣዲስ ተማሪዎች ባስመዘገቡት የመግቢያ ነጥብ

| የመግቢያ ነጥብ | ሴት | ወንድ | ድምር | መቶኛ | ከግማሽ በላይና በታች ያገኙ (%) |
|---|---|---|---|---|---|
| >=500 | 13 | 99 | 112 | 2.14 | |
| (500-450] | 114 | 166 | 280 | 5.34 | |
| (450-400] | 347 | 764 | 1111 | 21.18 | |
| (400-350] | 831 | 1590 | 2421 | 46.16 | 74.81 |
| (350-320] | 559 | 413 | 972 | 18.53 | |
| (320-302] | 286 | 62 | 348 | 6.63 | 25.17 |
| ድምር | 2150 | 3094 | 5244 | 99.98 | |

ከተመደቡት ተማሪዎች መግቢያ ነጥብ ማየት እንደሚቻለው ሶስት አራተኛ የሚሆኑት ተማሪዎች ከግማሽ በላይ ያገኙ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። ኣምስት መቶ እና ከዛ በላይ ያስመዘቡ ተማሪዎች ቁጥር ብቻ ከወሰድን ከመቶ በላይ ተማሪዎች ናቸው። ውጤታቸውን በመመልከት እስካሁን ድረስ ዩኒቨርሲቲው ይመደቡለት ከነበሩት ተማሪዎች ጋር ሲወዳደር ዘንድሮ የተሻለ ውጤት ያላቸው በርካታ ተማሪዎች መመደባቸውን ማየት ይቻላል። ይሄም ዩኒቨርሲቲው በኀበዝ ተማሪዎች ያለው ተመራጭነት እየጨመረ መምጣቱ ኣንድ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ለንፅፅር ያህል በ2007 ተመድበውልን የነበሩት ተማሪዎች ያስመዘገቡት ነጥብ መውሰድ ይቻላል። በ2007 ተመድበውልን ከነበሩት ኣዲስ ተማሪዎች ውስጥ ከ350 በታች ያገኙት 61% ነበሩ። ይህም ማለት ውጤታቸው ከግማሽ በታች የነበሩ (የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና የሚታረመው ከ700 ነው) ተማሪዎች የቱን ያህል ብዛት እንደነበረው የሚያሳይ ነው። በሌላ በኩል ከግማሽ በላይ የመግብያ ነጥብ የነበራቸው 39% ብቻ ነበሩ ማለት ነው። በ2008 ከግማሽ በላይ መግቢያ ውጤት ያመጡት ደግሞ 75% ነው። 500 እና ከዛ በላይ ያመጡትን ስናነፃፅር ደግሞ በ2007 የነበሩት 32 ብቻ ሲሆኑ በ2008 ግን 112 ናቸው። የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት ብቻውን የተማሪዎችን ችሎታ ሙሉ ለሙሉ የሚያሳይ እና በዩኒቨርሲቲ የሚያገኙትን ውጤት ለብቻው የሚወስን ባይሆንም (ምክንያቱም በዩኒቨርሲቲ ቆይታ የሚደረገው ጥረት ትልቅ ድርሻ ሊኖረው ይችላል) የተማሪዎችን ውጤት በመመሰን ከፍተኛ ሚና ካላቸው ነገሮች ውስጥ ኣንዱ መሆኑ ግን እሙን ነው።

ከ2008 ሁለተኛ ሰሚስተር ጀምሮ በተለይ በአንደኛ አመት ተማሪዎች ላይ አገልግሎት እንዲውል የተደረገው ያዋልነው የረጂስትራር በ2008 የትምህርት ዘመን ኣንደኛ ሰሚስተር ላይ ተመዝግበው በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርቧል። አዲስ የተመደቡት ተማሪዎች በሙሉ ላይመዘገቡ እንደሚችሉ የእስካሁን ልምዳችን የሚያሳይ ሲሆን ይሄንን ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል። ለምሳሌ በኣመቱ ከተመደቡልን 45 የኤርትራ ተማሪዎች ተመዝግበው ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙት 37 ናቸው። በተመሳሳይ መልኩ ኣዲስ ከተመደቡልን 32 የሶማልያ ተማሪዎች ውስጥ ተመዝግበው ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙት 27 ናቸው። ሌላው ግምት

ውስጥ መግባት ያለበት ባለፉት የትምህርት ኣመታት በተለያየ ምክንያት ትምህርት ኣቋርጠው የነበሩ ተማሪዎች ዘንድሮ በየሚመለከታቸው ኣመት በዳግመ ቅበላ (Readmission) ተመዝግበው በመማር ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ነው።

በሚቀጥለው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው በትምህርት አመቱ ሁለተኛ ሰሚስተር ተመዝግበው በትምህርት ላይ ያሉት የቅድመ ምረቃ መደበኛ ተማሪዎች ብዛት 12696 ነው። ከዚህ ቁጥር ውስጥ የሴት ተማሪዎች ብዛት 5149 (ወይም 40.56%) ሲሆን የወንድ ተማሪዎች ብዛት ደግሞ 7547 (ወይም 59.44%) ነው። በየትምህርት ክፍሉ ያለው የተማሪዎች ብዛት ዝርዝር በሪፖርቱ መጨረሻ Appendix 1 ላይ የተቀመጠውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 3. በ2008 ሁለተኛ ሰሚስተር በየኮሌጁ ተመዝግበው በመማር ላይ የሚገኙ መደበኛ ተማሪዎች (ቅድመ ምረቃ)

| College | Year I | | | Year II | | | Year III | | | Year IV | | | Year V | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T |
| College of Enginering and Technology | 1234 | 598 | 1832 | 900 | 667 | 1567 | 1032 | 371 | 1403 | 676 | 224 | 900 | 141 | 136 | 277 | 3983 | 1996 | 5979 |
| College of Natural and Computational Sciences | 146 | 324 | 470 | 269 | 95 | 364 | 115 | 246 | 361 | 24 | 7 | 31 | | | | 554 | 672 | 1226 |
| College of Medical and Health Sciences | 326 | 182 | 508 | 166 | 161 | 327 | 186 | 68 | 254 | 91 | 35 | 126 | | | | 769 | 446 | 1215 |
| College of Agriculture and Environmental Science | 268 | 254 | 522 | 120 | 117 | 237 | 89 | 58 | 147 | | | | | | | 477 | 429 | 906 |
| College of Business and Economics | 520 | 353 | 873 | 236 | 472 | 708 | 448 | 186 | 634 | | | | | | | 1204 | 1011 | 2215 |
| College of Social Sciences and Humanities | 194 | 277 | 471 | 173 | 177 | 350 | 193 | 141 | 334 | | | | | | | 560 | 595 | 1155 |
| **Total** | **2688** | **1988** | **4676** | **1864** | **1689** | **3553** | **2063** | **1070** | **3133** | **791** | **266** | **1057** | **141** | **136** | **277** | **7547** | **5149** | **12696** |

የቅድመ ምረቃ መደበኛ ተማሪዎች በ70 – 30 ቀመር መሰረት ተሰልቶ ሲቀመጥ በሚከተለው ሰንጠረዥ የተመለከተውን ይመስላል። በድምሩ ሲታይ ከባንድ አንድ እስከ አራት (ማለትም ተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ) ያሉት ተማሪዎች ብዛት 9677 (ወይም 74%) ሲሆን በባንድ አምስት እና ስድስት (ማህበራዊ ሳይንስ) ያሉት ተማሪዎች ብዛት ደግሞ 3419 (26%) ነው።

ሰንጠረዥ 4. የ70፤30 ስርጭት (መደበኛ ተማሪዎች) - ቅድመ ምረቃ ነባር ተማሪዎች ብቻ

| ኮሌጅ | ወ | ሴ | ድ | መቶኛ | 70 - 30 ቀመር |
|---|---|---|---|---|---|
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ (ባንድ 1) | 3983 | 1996 | 5979 | 47.1 | |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ (ባንድ 2) | 554 | 672 | 1226 | 9.7 | |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ (ባንድ 3) | 769 | 446 | 1215 | 9.6 | |
| ግብርናና አከባቢያዊ ሳይንስ (ባንድ 4) | 477 | 429 | 906 | 7.1 | 73.5 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ (ባንድ 5) | 1204 | 1011 | 2215 | 17.4 | |
| ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ (ባንድ 6) | 560 | 595 | 1155 | 9.1 | 26.5 |
| ድምር | 7547 | 5149 | 12696 | 100.0 | 100 |
| መቶኛ | 59.4 | 40.6 | 100 | | |

በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲሟላ የሚፈለገው የተማሪዎች ስብጥር ከተማሪዎቹ 70% በተፈጥሮ ሳይንስ መስኮች (ባንድ 1፡ 2፡ 3 እና 4) እንዲሆኑ ሲሆን የተቀሩት 30% ደግሞ በማህበራዊ ሳይንስ መስኮች (ማለትም ባንድ 5 እና 6) እንዲሆኑ ነው። ከላይ በሰንጠረዡ እንደተቀመጠው በየባንዱ በዩኒቨርሲቲው ያለው ስብጥር የሚያሳየው በኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ (ባንድ 1) 47.1%፤ በተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ (ባንድ 2) 9.7%፤ በህክምናና ጤና ሳይንስ (ባንድ 3) 9.6%፤ በግብርናና አከባቢ ሳይንስ (ባንድ 4) 7.1% ፤በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ (ባንድ 5) 17.4%፤ እና በሌሎች ህብረተሰብ ሳይንስ (ባንድ 6) 9.1% ነው። በድምሩ ሲወሰድ ደግሞ ከጠቅላላው ተማሪዎች ውስጥ በተፈጥሮ ሳይንስ መስክ 73.5% በማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ደግሞ 26.5% ተማሪዎች ይገኛሉ ማለት ነው። በ70–30 ቀመር መሰረት በዩኒቨርሲቲው ያለው የተማሪዎች ስብጥር ወደ ተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፉ በጎላ መልኩ ያደላ እንደሆነ ማየት ይቻላል። በየባንዱ ሲታይ ደግሞ በባንድ አንድ ያሉት ተማሪዎች ብዛት 47% ስለሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚፈለገው የ40% ድርሻ የበለጠ እንደሆነ ማየት ይቻላል። በባንድ ሁለት መኖር የሚገባው የተማሪ ቁጥር 20% ሲሆን በዚሁ ባንድ በዩኒቨርሲቲው ያለው የተማሪ ብዛት 9.7% ብቻ ነው። ስለዚህ በዚሁ ባንድ ያለው የተማሪ ብዛት ከሚፈለገው ቁጥር በታች መሆኑ መገንዘብ አያዳግትም። በሌላ በኩል ደግሞ በህክምናና ጤና ሳይንስ መስክ (ባንድ ሶስት) እንዲኖር የሚጠበቀው 5% ሲሆን በዩኒቨርሲቲው ያለው ተማሪ ብዛት ግን ከሚጠበቀው በላይ ማለትም 9.6% ነው። በተመሳሳይ መልኩ በባንድ 5 ያለው ተማሪ ከኮታው (ማለትም 5%) በላይ መሆኑ ከሰንጠረዡ ማየት ይቻላል። በማህበራዊ ዘርፉ ሲታይ ደግሞ በባንድ አምስት ያለው የተማሪ ብዛት ለኮታው (ማለትም 20%) የተጠጋ ሲሆን በባንድ 6 ያለው ተማሪ ብዛት ደግሞ ከኮታው (10%) ብዙም ያልራቀ መሆኑ መገንዘብ ይቻላል። ለማንኛውም አጠቃላይ ቀመሩ በአገር ደረጃ እንጂ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ብቻ የማይወሰን ስለሆነ የአንዱን ጉድለት ወይም መብዛት በሌላው ዩኒቨርሲቲ ሊጣጣም የሚችል መሆኑ መገንዘብ ያሻል።

ዩኒቨርሲቲው በ2008 የመጀመርያው ሰሚስተር ተመዝግበው በመማር ላይ ከነበሩት 13091 ተማሪዎች ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ብዛት 545 ሲሆን ዝርዝሩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 5. በተለያየ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ብዛት

| | አንደኛ አመት | | | ሁለተኛ አመት | | | ሶስተኛ አመት | | | አራተኛ አመት | | | አምስተኛ አመት | | | ጠቅላላ ድምር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ዓይነት** | **ወ** | **ሴ** | **ድ** | **ወ** | **ሴ** | **ድ** | **ወ** | **ሴ** | **ድ** | **ወ** | **ሴ** | **ድ** | **ወ** | **ሴ** | **ድ** | **ወ** | **ሴ** | **ድ** | **መቶኛ** |
| **ተፈቅዶላቸው ያቋረጡ** (Withdrawals) | 42 | 40 | 82 | 38 | 56 | 94 | 18 | 11 | 29 | 3 | 1 | 4 | 1 | 2 | 3 | 102 | 110 | 212 | **1.62** |
| **ሳያስፈቅዱ ያቋረጡ** (Dropouts) | 26 | 30 | 56 | 16 | 11 | 27 | 5 | 1 | 6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 47 | 42 | 89 | **0.68** |
| **በትምህርት ድክመት ያቋረጡ** (Dismissals) | 15 8 | 196 | 354 | 42 | 73 | 115 | 15 | 19 | 34 | 5 | 8 | 13 | 0 | 0 | 0 | 220 | 296 | 516 | **3.94** |
| **ድምር** | **226** | **266** | **492** | **96** | **140** | **236** | **38** | **31** | **69** | **8** | **9** | **17** | **1** | **2** | **3** | **369** | **448** | **817** | **6.26** |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው በአመቱ በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርት ያቋረጡ የቅድመ ምረቃ መደበኛ ተማሪዎች ብዛት 817 (ወይም በአንደኛ ሰሚስተር በመማር ላይ ከነበሩት 13091 ተማሪዎች ውስጥ 6.26%) ነው። ዩኒቨርሲቲው በአመቱ የያዘው እቅድ ከ5% በታች እንዲሆን የነበረ ሲሆን ይሄንን ታርጌቱን ሊያሳካ እንዳልቻለ መገንዘብ ይቻላል። በተለያየ ምክንያት ካቋረጡት ውስጥ አብዛኛዎቹ ማለትም 516 ተማሪዎች (ወይም 3.94%) በትምህርት ድክመት ያቋረጡ ናቸው። በትምህርት ድክመትም (academic dismissals) ይሁን አስፈቅደው (withdrawals) ያቋረጡት ተማሪዎች ከአንድ ሰሚስተር እረፍት በኋላ ተመልሰው ትምህርታቸውን መከታተል የሚችሉ ቢሆንም (የደከሙባቸውን የትምህርት አይነቶች ተመልሰው ለመማር ስለሚችሉም ድክመታቸውን ለማሻሻሽ እድል ያገኛሉ) የማቋረጡ መጠን ከፍተኛ ስለሆነ ዩኒቨርሲቲው በትኩረት ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑ ግልፅ ነው።

ዩኒቨርሲቲው ከመደበኛ ተማሪዎች በተጨማሪ የማታ ተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች እና የክረምት ተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች ያሉት ሲሆን በሚከተለው ሰንጠረዥ በዝርዝር እንደተቀመጠው በ2008 ሁለተኛ ሰሚስተር በቅድመ ምረቃ መርሃ ግብር በማታ ተከታታይ መርሃ ግብር በድምሩ 1174 (691 ወንድ እና 486 ሴት) ተማሪዎች ተመዝግበው በመማር ላይ ይገኛሉ። ዝርዝሩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ 6. የማታ ተከታታይ ተማሪዎች (2008 ሁለተኛ ሰሚስተር)

| College | Department/Program | Undergraduate EVENING | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | YEAR I | | | YEAR II | | | Year III | | | Year IV | | | Year V | | | Total | | |
| | | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T |
| | Information Technology | | | | | | | 5 | 12 | 17 | | | | | | | 5 | 12 | 17 |
| | Civil engineering | | | | 21 | 1 | 22 | 27 | 3 | 30 | 28 | 1 | 29 | 50 | 4 | 54 | 126 | 9 | 135 |
| | Construction Technology and Mgt. | | | | | | | 19 | | 19 | | | | | | | 19 | | 19 |
| | Electrical and Computer engineering | | | | | | | | | | | | | 15 | 1 | 16 | 15 | 1 | 16 |
| CET | **SUB TOTAL** | | | | **21** | **1** | **22** | **51** | **15** | **66** | **28** | **1** | **29** | **65** | **5** | **70** | **165** | **22** | **187** |
| | Health Officer | | | | 13 | 9 | 22 | 20 | 14 | 34 | | | | | | | 33 | 23 | 56 |
| | Nursing | 18 | 28 | 46 | 18 | 14 | 32 | 14 | 18 | 32 | 15 | 12 | 27 | | | | 65 | 72 | 137 |
| | Pharmacy | 40 | 17 | 57 | | | | | | | | | | | | | 40 | 17 | 57 |
| CMHS | **SUB TOTAL** | **58** | **45** | **103** | **31** | **23** | **54** | **34** | **32** | **66** | **15** | **12** | **27** | | | | **138** | **112** | **250** |
| | Accounting and Finance | 141 | 158 | 299 | 88 | 85 | 173 | 40 | 30 | 70 | 33 | 21 | 54 | | | | 302 | 294 | 596 |
| | Management | 48 | 29 | 77 | 23 | 20 | 43 | 15 | 9 | 24 | | | 0 | | | | 86 | 58 | 144 |
| CBE | **SUB TOTAL** | **189** | **187** | **376** | **111** | **105** | **216** | **55** | **39** | **94** | **33** | **21** | **54** | | | | **388** | **352** | **740** |
| **TOTAL** | | **247** | **232** | **479** | **163** | **129** | **292** | **140** | **86** | **226** | **76** | **34** | **110** | **65** | **5** | **70** | **691** | **486** | **1177** |

ከላይ በሰንጠረዥ እንደሚታየው የማታ ቅድመ ምረቃ ተከታታይ ትምህርት በሶስት ኮሌጆችና በዘጠኝ ፕሮግራሞች በመካሄድ ላይ ይገኛል። በኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ ስር በአራት ፕሮግራሞች (ሲቪል ኢንጂነሪንግ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እና ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ)፤ በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ስር በሶስት ፕሮግራሞች (ሄልዝ ኦፊሰር፣ ነርሲንግና ፋርማሲ) እንዲሁም በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ በሁለት ፕሮግራሞች (አካውንቲንግና ፋይናንስ እና ማኔጅመንት) በመካሄድ ላይ ይገኛል። በዚሁ መርሃ ግብር ላይ በ2007 ከነበሩት የተማሪዎች ቁጥር (ማለትም 923) ጋር ሲነፃፀር የዘንድሮው (ማለትም 1177) የ254 ጭማሪ አለው። ከዚይ መረዳት እንደሚቻለው የማታ ቅድመ ምረቃ ተከታታይ ትምህርት እያሳየ ያለው መስፋፋት ውሱን መሆኑን ነው። በአንደኛ ሰሚስተር የነበረው የማታ ቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ብዛት 1216 የነበረ ሲሆን በሁለተኛ ሰሚስተር የተመዘገቡት ተማሪዎች በአንደኛ ሰሚስተር ከነበሩት በ39 የቀነሰ መሆኑን ያሳያል። ይሄም ማለት 39 (ወይም 3.2%) የማታ ቅድመ ምረቃ ተማሪዎች በተለያየ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

የድህረ ምረቃ ትምህርት በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው 2007 ላይ በሁለት ፕሮግራሞች (Master of Accounting and Finance, and Master of Business Administration) የመደበኛና የማታ ተከታታይ ተማሪዎችን በመቀበል የጀመረ ሲሆን 2008 ላይ ፕሮገራሞቹ ወደ ስድስት ያደጉ ሲሆን በመደበኛው እና በተከታታይ ያሉን ተማሪዎች ቁጥር በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርቧል። ከሰንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው ዩኒቨርሲቲው ያሉት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት 203 ነው (53 የመደበኛ ድህረ ምረቃ እና 150 የተከታታይ ድህረ ምረቃ)። በአንደኛ ሰሚስተር ይማሩ የነበሩት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ብዛት 218 የነበረ ሲሆን በሁለተኛ ሰሚስተር ተመዝግበው በመማር ላይ ከሚገኙት በ15 ዝቅ ያለ ነው። ይህም ማለት 15 የድህረ ምረቃ ተማሪዎች (ወይም 7%) በተለያየ ምክንያት ትምህርት አቋርጠዋል ማለት ነው። ያቋረጡት ተማሪዎች በሙሉ በተከታታይ ትምህርት ከሚማሩት ውስጥ ብቻ ስለሆነ ከመደበኛው ትምህርት ያቋረጡ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች የሉም። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ካሉት ስድስት ኮሌጆች ውስጥ አራቱ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ያላቸው ሲሆን እነሱም ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ (CET)፣ ግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ (CAES)፣ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ (CBE) እና ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ ኮሌጅ (CSSH) ናቸው። የድህረ ምረቃ ፕሮግራሙ የሚከናወነው በመደበኛ እና በማታ ተከታታይ መርሃ ግብር ሲሆን በመደበኛው 53 ተማሪዎች በማታ ተከታታይ 150 በድምሩ 203 ተማሪዎች አሉን። በ2007 ከነበረው ጋር ለማነፃፀር ያህል ያኔ የነበሩን ተማሪዎች 108 ሲሆን የዘንድሮው (203) ከአምናው (108) ጋር ሲነፃፀር የ95 ተማሪዎች ብልጫ አለው።

ሰንጠረዥ 7፤ የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞችና ተማሪዎች ብዛት (2008 ሁለተኛ ሰሚስተር)

| College | Department/Program | MASTER's Regular | | | | | | | | | MASTER's Evening | | | | | | | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | year I | | | Year II | | | Total | | | year I | | | Year II | | | Total | | | | | |
| | | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T |
| | Computer Science | 5 | 4 | 9 | | | | 5 | 4 | 9 | | | | | | | | | | 5 | 4 | 9 |
| | Information Technology | 8 | 1 | 9 | | | | 8 | 1 | 9 | | | | | | | | | | 8 | 1 | 9 |
| CET | SUB TOTAL | 13 | 5 | 18 | | | | 13 | 5 | 18 | | | | | | | | | | 13 | 5 | 18 |
| | Animal Productiona and Technology | 10 | | 10 | | | | 10 | | 10 | | | | | | | | | | 10 | | 10 |
| CAES | SUB TOTAL | 10 | | 10 | | | | 10 | | 10 | | | | | | | | | | 10 | | 10 |
| | Accounting and Finance | 3 | 1 | 4 | 1 | 1 | 2 | 4 | 2 | 6 | 14 | 3 | 17 | 16 | 3 | 19 | 30 | 6 | 36 | 34 | 8 | 42 |
| | Management | 5 | 0 | 5 | 9 | | 9 | 14 | | 14 | 34 | 4 | 38 | 57 | 2 | 59 | 91 | 6 | 97 | 105 | 6 | 111 |
| CBE | SUB TOTAL | 8 | 1 | 9 | 10 | 1 | 11 | 18 | 2 | 20 | 48 | 7 | 55 | 73 | 5 | 78 | 121 | 12 | 133 | 139 | 14 | 153 |
| | Sociology | 5 | | 5 | | | | 5 | | 5 | 14 | 3 | 17 | | | | 14 | 3 | 17 | 19 | 3 | 22 |
| CSSH | SUB TOTAL | 5 | | 5 | | | | 5 | | 5 | 14 | 3 | 17 | | | | 14 | 3 | 17 | 19 | 3 | 22 |
| Total | | 36 | 6 | 42 | 10 | 1 | 11 | 46 | 7 | 53 | 62 | 10 | 72 | 73 | 5 | 78 | 135 | 15 | 150 | 181 | 22 | 203 |

ሌላው በዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማር ሂደት የሚከናወነው የክረምት መርሃ ግብር ነው። የክረምት መርሃግብር ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን አንደኛው የዲግሪ ፕሮገራም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በመካሄድ ላይ የሚገኘው የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ (Post Graduate Diploma Teaching – PGDT) ፕሮግራም ነው። በድህረ ምረቃ ዲፕሎማ ፕሮግራም በመማር ላይ ያሉት በትምህርት ሚኒስቴር በመምህርነት ሞያ ተሰማርተው የሚገኙ ሲሆን ከየቦታው ተመልምለው የማስተማር ክህሎታቸውን ለማሳደግ አስፈላጊ የሆኑ ኮርሶች የሚወስዱበት ፕሮግራም ነው። የዲግሪ ፕሮግራሙ ራሱ በሁለት የተከፈለ ሲሆን አንደኛው የተለመደው ዲግሪ ፕሮግራም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከክልሉ የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርትና ስልጠና (TVET) ቢሮ ጋር በመተባበር በመካሄድ ላይ የሚገኘው በአገራችን በአይነቱ የመጀመርያ የሆነው የቴክኖሎጂ ባችለር ዲግሪ ፕሮግራም (Bachellor of Technology – Btech) ነው። በአጠቃላይ በክረምት መርሃ ግብር በመማር ላይ ያሉት ተማሪዎች ብዛት 3962 ሲሆን ከዚሁም ውስጥ የዲግሪ ፕሮግራም በመከታተል ላይ የሚገኙት 2697 ሲሆን የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ ፕሮግራም በመከታተል ላይ የሚገኙት ደግሞ 1265 ናቸው።

ዩኒቨርሲቲው በድምሩ 18038 ተማሪዎች ያሉት ሲሆን በየመርሃ ግብሩ ያለው የተማሪዎች ብዛት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ የቀረበውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 8. የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ብዛት በመርሃ ግብር

| | ቅድመ ምረቃ | | | ድህረ ምረቃ | | | ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፕሮግራም | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| መደበኛ | 7547 | 5149 | 12696 | 46 | 7 | 53 | 7593 | 5156 | 12749 |
| የማታ ተከታታይ | 691 | 486 | 1177 | 135 | 15 | 150 | 826 | 501 | 1327 |
| የክረምት ተከታታይ (ዲግሪ ፕሮግራም) | 2002 | 695 | 2697 | | | | 2002 | 695 | 2697 |
| የክረምት ተከታታይ (ፒጂዲቲ) | 835 | 430 | 1265 | | | | 835 | 430 | 1265 |
| ጠቅላላ ድምር | 11075 | 6760 | 17835 | 181 | 22 | 203 | 11256 | 6782 | 18038 |
| መቶኛ | | | 98.87 | | | 1.13 | 62.40 | 37.6 | 100 |

**2.2 መምህራንና የአካዳሚክ ቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች**

ዩኒቨርሲቲው 2004 ሕዳር ላይ የመጀመርያ ባች ተማሪዎችን ተቀብሎ በሚያስተናግድበት ወቅት የነበሩት የመምህራን ብዛት 94 የነበረ ሲሆን በዚሁ ወቅት የነበሩት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት ደግሞ 109 ነበር። በ2008 የመምህራን ብዛት 856 የደረሰ ሲሆን ከዚህ ቁጥር ውስጥ በስራ ላይ ያሉት የአገር ውስጥ መምህራን 522፤ ትምህርት ላይ ያሉት መምህራን 296 እና የውጭ መምህራን ደግሞ 38 ናቸው። በየኮሌጁ በስራ ላይ ያሉት የአገር ውስጥ መምህራን በሚከተለው ሰንጠረዥ የተቀመጠውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 9፤ ስራ ላይ ያሉት የአገር ውስጥ መምህራን

| ኮሌጅ | BA/BSC (Assts.) | | | MA/MSc/MD/DVM | | | PhD | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | M | F | T | M | F | Total | M | M | F | T |
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ | 157 | 22 | 179 | 33 | 3 | 36 | | 190 | 25 | 215 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 14 | | 14 | 71 | 8 | 79 | 1 | 86 | 8 | 94 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | 15 | 6 | 21 | 33 | 4 | 37 | | 48 | 10 | 58 |
| ግብርናና አከባቢ ሳይንስ | 1 | 1 | 2 | 23 | 4 | 27 | 1 | 25 | 5 | 30 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 6 | | 6 | 32 | 4 | 36 | 1 | 39 | 4 | 43 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ | 20 | 7 | 27 | 49 | 6 | 55 | | 69 | 13 | 82 |
| ድምር | 213 | 36 | 249 | 241 | 29 | 270 | 3 | 457 | 65 | 522 |
| መቶኛ | | | 47.70 | | | 51.72 | 0.57 | 87.55 | 12.45 | 100 |

በሰንጠረዡ እንደሚታየው ስራ ላይ ካሉት የአገር ውስጥ መምህራን ውስጥ 48% ያህሉ የመጀመርያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን 52% የሚሆኑት ደግሞ ሁለተኛ ዲግሪና ከዛ በላይ ያላቸው ናቸው። ዩኒቨርሲቲዎች ሊደርሱበት ይገባል ተብሎ ከተያዘው የ75% (ሁለተኛ ዲግሪ) እና የ25% (ሶስተኛ ዲግሪ) ታርጌት ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለን መሆኑ ማየት የሚያዳግት አይደለም። በርግጥ ስራ ላይ ያሉት የውጭ ሃገር መምህራን ቁጥር ሲጨመርበት ስብጥሩ በተወሰነ መልኩ ይሻሻላል። በዚሁም መሰረት የውጭ አገር መምህራን ሲጨመርበት በስራ ላይ ካሉት መምህራን ውስጥ 45.5% የመጀመርያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን 55.5% ደግሞ ሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ናቸው። ይህ ስብጥርም ቢሆን በመጠኑ የተሻለ ቢሆንም ወደሚፈለገው ታርጌት ለመድረስ ግን ገና ብዙ ርቀት እንደሚቀር መገንዘብ የሚከብድ አይሆንም። ስራ ላይ ያሉት የአገር ውስጥ መምህራን ብቻ በመውሰድ የዩኒቨርሲቲው ሴት መምህራን ብዛት 65 ሲሆን በመቶኛ ሲገለፅ ደግሞ 12.45% ብቻ መሆኑን ያሳያል። የሴት መምህራን ቁጥር በተመለከተም ከሚፈለገው መጠን በታች መሆኑ በግልፅ የሚታይ ስለሆነ የመፍትሄ አቅጣጫ መቀየስ የሚያስፈልግ መሆኑ ለመገንዘብ የሚከብድ አይደለም።

በየኮሌጁ ያሉት ጠቅላላ የመምህራን ብዛት (ስራ ላይ ያሉት የአገር ውስጥ እና የውጭ መምህራን እንዲሁም ትምህርት ላይ ያሉት መምህራን በሚያካትት መልኩ) በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 10፤ የዩኒቨርሲቲው መምህራን ብዛት (ስራ ላይ ያሉ እና ትምህርት ላይ ያሉ)

| ኮሌጅ | ስራ ላይ ያሉ የአገር ውስጥ | | | ስራ ላይ ያሉ የውጭ | | | ትምህርት ላይ ያሉ | | | ጠቅላላ ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ | 190 | 25 | 215 | 13 | 0 | 13 | 117 | 23 | 140 | 320 | 48 | 368 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 86 | 8 | 94 | 7 | 0 | 7 | 28 | 2 | 30 | 121 | 10 | 131 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | 48 | 10 | 58 | 3 | 0 | 3 | 50 | 7 | 57 | 101 | 17 | 118 |
| ግብርናና አከባቢ ሳይንስ | 25 | 5 | 30 | 1 | 0 | 1 | 6 | 2 | 8 | 32 | 7 | 39 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 39 | 4 | 43 | 6 | 1 | 7 | 23 | 1 | 24 | 68 | 6 | 74 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ | 69 | 13 | 82 | 6 | 1 | 7 | 30 | 7 | 37 | 105 | 21 | 126 |
| ድምር | 457 | 65 | 522 | 36 | 2 | 38 | 254 | 42 | 296 | 747 | 109 | 856 |
| መቶኛ | | | 60.98 | | | 4.44 | | | 34.58 | 87.27 | 12.73 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደሚታየው ዩኒቨርሲቲው በጠቅላላ ያሉት የመምህራን ብዛት 856 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የውጭ አገር መምህራን ብዛት 38 (ማለትም 35 የህንድ 2 የፊሊፒንስ እና 1 የጀርመን) ነው። ከጠቅላላው መምህራን 296 የሚሆኑት ትምህርት ላይ ያሉ ሲሆን የተቀሩት **560** (522 የአገር ውስጥ እና 38 የውጭ አገር) ደግሞ ስራ ላይ ያሉ ናቸው። ትምህርት ላይ ካሉ መምህራን ውስጥ 229 የሚሆኑት ለሁለተኛ ዲግሪ በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 221 (185 ወንድ እና 36 ሴት) አገር ውስጥ በመማር ላይ ይገኛሉ፤ የተቀሩት 9 ደግሞ ውጭ አገር በመማር ላይ የሚገኙ ናቸው። ለዶክትሬት ዲግሪ (ስፔሻላይዜሽን ጨምሮ) በመማር ላይ የሚገኙ መምህራን ብዛት 66 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አገር ቤት በመማር የሚገኙት 52 (48 ወንድ እና 4 ሴት መምህራን - ከዚህ ቁጥር ውስጥ 25 መምህራን ለስፔሻላይዜሽን ዲግሪ በመማር ላይ ይገኛሉ) ናቸው፤ ውጭ ኣገር ለሶስተኛ ዲግሪ (ስፔሻላይዜሽን ጨምሮ) በመማር ላይ የሚገኙት ደግሞ 14 (12 ወንድ እና 2 ሴት መምህራን) ናቸው። ትምህርት ላይ ያሉት የዩኒቨርሲቲው መምህራን ትምህርታቸውን ጨርሰው ሲመለሱ የመምህራን የትምህርት ደረጃ ስብጥር ላይ ጥሩ ለውጥ እንደሚያመጣ እሙን ነው።

ቀደም ብሎ የተቀመጠው የተማሪዎች ብዛትና ከላይ የተመለከተው የመምህራን ብዛት በመጠቀም **የመምህር–ተማሪ ጥምርታ** ወይም Teacher-Student Ratio ማስላት ይቻላል። በዚሁም መሰረት፤

1. በስራ ላይ ያሉት መምህራንና መደበኛ (ቅድመ እና ድህረ ምረቃ) ተማሪዎች በመውሰድ፤ በስራ ላይ ያሉት መምህራን (የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር) ቁጥር 560 ሲሆን የመደበኛ ተማሪዎች ብዛት ደግሞ 12749 (12696 ቅድመ ምረቃ እና 53 ድህረ ምረቃ) ነው። በዚሁም መሰረት በዩኒቨርሲቲው ያለው የመምህር ተማሪ ጥምርታ (Teacher-Student Ratio) **22.76** ይሆናል። ይህ ጥምርታ የኣካዳሚክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን (Technical Assistants) የማያካትት ነው።
2. በተራ ቁጥር ኣንድ በተቀመጠው ሆኖ የኣካዳሚክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በማካተት፤ በዚሁ ስሌት መሰረት ዩኒቨርሲቲው 46 የኣካዳሚክ ቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ስላሉት ይሄንን በማካተት የሚኖረው የመምህር ተማሪ ጥምርታ **21.04** ነው።
3. የዩኒቨርሲቲው ጠቅላላ መምህራን (ስራ ላይ ያሉ እና ትምህርት ላይ ያሉ) እና መደበኛ ተማሪዎችን (ቅድመ እና ድህረ ምረቃ) በመውሰድ፤ የዩኒቨርሲቲው ጠቅላላ መምህራን ብዛት 856 ስለሆነ (560 ስራ ላይ ያሉ እና 296 ትምህርት ላይ ያሉ) እና የመደበኛ ተማሪዎች ብዛት ደግሞ 12749 ስለሆነ የመምህር ተማሪ ጥምርታ **14.89** መሆኑን ያመለክታል። በመምህራን ቁጥር ላይ የኣካዳሚክ ቴክኒክ ድጋፍ ሰጪዎች ከተጨመሩ ደግሞ የመምህር ተማሪ ጥምርታ ወደ **14.13** ዝቅ ይላል።
4. ጠቅላላ መምህራን እና ጠቅላላ ተማሪዎች (መደበኛና ተከታታይ) በመውሰድ፤ በዚሁ ስሌት መሰረት የመምህራን ብዛት 856 ሲሆን የተማሪዎች ብዛት ደግሞ 18038 ስለሆነ የመምህር ተማሪ ጥምርታ **21.07** ይሆናል። በመምህራን ብዛት የቴክኒክ ደጋፊዎችን ስንጨምር የሚኖረው የመምህር ተማሪ ጥምርታ ወደ **20** ዝቅ ይላል።

የዩኒቨርሲቲው መምህራንን በተመለከተ ኣሃዛዊ መረጃ ከላይ የቀረበ ሲሆን በየኮሌጁ ያሉት የኣካዳሚክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች (Technical Assistants) ብዛት ደግሞ በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 11፤ የአካዳሚክ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

| ኮሌጅ | ወ | ሴ | ድ |
|---|---|---|---|
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ | 14 | 5 | 19 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 16 | 3 | 19 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | 2 | 1 | 3 |
| ግብርናና አከባቢ ሳይንስ | 4 | | 4 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | | 1 | 1 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ | | | |
| ድምር | 36 | 10 | 46 |

## 2.3 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

ዩኒቨርሲቲው የመጀመርያ ባች ተማሪዎችን በተቀበለበት ህዳር 2004 የነበሩት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት 109 ብቻ ነበር። በ2007 ዩኒቨርሲቲው የነበሩት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት 1176 (ማለትም 1141 ቋሚ እና 35 የኮንትራት) ሲሆን በ2008 አሁን ያሉን የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት 1179 (ማለትን 1151 ቋሚ እና 28 የኮንትራት) ደርሷል። በ2004 መጨረሻ ላይ ተዘጋጅቶ የነበረው የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መዋቅር ለሶስት አመታት እንዲያገለግል ታስቦ የተዘጋጀ ነበር። በዚሁ መዋቅር የተፈቀደው የሰራተኛ ብዛት 1186 የነበረ ሲሆን የፅዳት ስራውን ወደ ውጭ በመውጣቱ (Outsource ስለተደረገ) ምክንያት የተቀጠሩት ሰራተኞች ከዚህ ቁጥር ያነሰ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ዩኒቨርሲቲው ካደረገው መስፋፋት ጋር ተያይዞ በተለይም በምግብ ቤት አከባቢ፤ በተማሪዎች መኝታ ቤት አከባቢ (ፕሮክተሮች)፤ በረጂስትራር፤ በሾፌሮች እና በሌሎች ክፍሎች ተፈቅዶልን በነበረው መዋቅር ያልተካተቱ ሰራተኞች ስለነበሩ ተጨማሪ የሰራተኞች ቁጥር እንዲፈቀድልን ጠይቀን ስለተፈቀደልን ተጨማሪ ቅጥሮችን አካሂደናል።

እስከ መጋቢት 2008 ድረስ በዩኒቨርሲቲው የተቀጠሩ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት በሚከተሉት ሁለት ሰንጠረዦች የተመለከተውን ይመስላል። ይህ ቁጥር የፅዳት ስራው ወደ ውጭ በመውጣቱ ምክንያት (outsource) በከተማው ትምህርት ጨርሰው ለተደራጁት የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋም እንዲሰጥ ስለተደረገ፤ በተጨማሪም የቆሻሻ ማስወገድ ስራም በተመሳሳይ መልኩ ወደ ውጭ ስለወጣ በነዚህ ስራዎች በመስራት ላይ የሚገኙት ሰራተኞች በዩኒቨርሲቲው የሰራተኞች አሃዝ የተካተተ አይደለም።

ሰንጠረዥ 12. ቋሚ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

| ተ.ቁ. | ፅህፈት ቤት | እስከ መጋቢት 30 የተቀጠሩ ቋሚ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ፕረዚደንት ፅ/ቤት | 1 | 3 | 4 |
| 2 | እቅድና ተቋማዊ ማሻሻያ ፅ/ቤት | 2 | 2 | 4 |
| 3 | ሕዝንብና የውጭ ግንኙነት ፅ/ቤት | 2 | 1 | 3 |
| 4 | ውስጥ ኦዲት ፅ/ቤት | 2 | 3 | 5 |
| 5 | ስርአተ ፆታ ፅ/ቤት | 2 | 1 | 3 |
| 6 | ህግ ፅ/ቤት | 1 | 2 | 3 |
| 7 | ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና መከታተያ ዳይሬክቶሬት | 2 | 1 | 3 |
| 8 | አካዳሚክና ምርምር ም/ፕረዚዳንት ፅ/ቤት | 2 | 1 | 3 |
| 9 | ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ | 1 | 6 | 7 |
| 10 | ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ | 2 | 10 | 12 |
| 11 | ተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ | 1 | 10 | 11 |
| 12 | ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ | 1 | 10 | 11 |
| 13 | ግብርና ኮሌጅ | 1 | 5 | 6 |
| 14 | ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ | 0 | 7 | 7 |
| 15 | ሬጂስትራር | 4 | 23 | 27 |
| 16 | ቤተመፃህፍትና ዶኩመንቴሽን | 83 | 104 | 187 |
| 17 | ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ማእከል | 7 | 2 | 9 |
| 18 | አስተዳደርና ልማት ም/ፕረዚዳንት ፅ/ቤት | 2 | 2 | 4 |
| 19 | ሰው ሃብት ልማት ማእከል | 6 | 9 | 15 |
| 20 | ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት | 16 | 12 | 28 |
| 21 | የፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት | 10 | 12 | 22 |
| 22 | መሰረታዊ አገልግሎት ማእከል | 161 | 23 | 184 |
| 23 | የተማሪዎች ዲን ፅ/ቤት | 7 | 2 | 9 |
| 24 | የተማሪዎች መኝታ ቤትና መዝናኛ አገልግሎት | 43 | 42 | 85 |
| 25 | ተማሪዎች ዲን (ምግብ ቤት ሰራተኞች) | 70 | 562 | 632 |
| 26 | ተማሪዎች ዲን (ክሊኒክ ሰራተኞች) | 9 | 7 | 16 |
| 27 | የዩኒቨርሲቲ ኢንዳስትሪ ትስስር ዳይሬክቶሬት | 0 | 1 | 1 |
| 28 | የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት | 0 | 1 | 1 |
| 29 | የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት | 1 | 1 | 2 |
| ጠ/ድምር | | 439 | 865 | 1304 |

ከላይ በተመለከተው ሰንጠረዥ እንደሚታየው ዩኒቨርሲቲው ታህሳስ 30/2008 ስራ ላይ የነበሩት ቋሚ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች 1304 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ በጣም አብዛኛዎቹ (ማለትም 632 የሚሆኑት ወይም 48.5%) በምግብ ቤት አከባቢ በመስራት ላይ የሚገኙ ናቸው። በስራ ላይ ካሉት ቋሚ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በተጨማሪ 2 ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ትምህርት ላይ ስላሉት ዩኒቨርሰቲው በድምሩ 1306 ያህል ቋሚ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ነው ያሉት። ከቋሚ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ውስጥ የሚበልጡት ማለትም 865 (ወይም 66.23%) ሴት ሰራተኞች ናቸው።

ሰንጠረዥ 13፤ የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

| ተ.ቁ. | አይነት | እስከ መጋቢት 30 የተቀጠሩ የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ግንባታ ፕሮጀክት ፅ/ቤት | 11 | 3 | 14 |
| 2 | ጥበቃ | 10 | 0 | 10 |
| 3 | ሹፌር | 6 | 0 | 6 |
| ድምር | | 27 | 3 | 30 |

የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ጨምሮ ዩኒቨርሲቲው በድምሩ እስከ ታህሳስ 2008 ድረስ የነበሩት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቁጥር 1336 ነው። በፆታ ስብጥር ሲታይ ደግሞ ከጠቅላላው ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ውስጥ **64.97%** ሴት ሰራተኞች ናቸው።

## 3. ለ2008 የተፈቀደልን በጀትና አጠቃቀሙ

ዩኒቨርሲቲው ለ2008 የሚያስፈልገውን በጀት በ2007 ላይ ካቀረበ በኋላ በመደበኛና በካፒታል ተከፋፍሎ የኣመቱ በጀት ተፈቅዶለት ዩኒቨርሲቲው ለኣመቱ በእቅድ የያዛቸውን ተግባራት በማከናወን ላይ ይገኛል። በተለይ ካፒታል ባጀቱ ዩኒቨርሲቲው ሊሰራው ከያዘው እቅድ ጋር ሲተያይ ሊያንስ እንደማይችል ቀደም ብሎ ግምት ተወስዶበት ነበር። እስከ መጋቢት 30 የነበረው የስድስት ወራት የበጀት አጠቃቀም እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 3.1. መደበኛ በጀት

ለ2008 የተፈቀደልን መደበኛ ባጀት በፕሮግራም ባጀት አደላደል መሰረት ለአራት ፕሮግራሞች ማለትም ለፕሮግራም አንድ ወይም ለአስተዳደር ስራዎች (131083440.00)፤ ለፕሮግራም ሁለት ወይም አካዳሚክ ነክ ስራዎች (113737800.00)፤ ለፕሮግራም ሶስት ወይም ለጥናትና ምርምር (5820200.00)፤ እና ለፕሮግራም አራት ወይም ለማህበረሰብ አገልግሎት (2753000.00) በድምሩ ብር 253394440.00 ተመድቦልናል። ለ2007 ተፈቅዶልን ከነበረ መደበኛ ባጀት (ማለትም 227658160.00) ጋር ሲነፃፀር የ2008 መደበኛ ባጀት በ25736280.00 ብር ብልጫ ያለው ነው። ይህም ማለት የ2008 ባጀት በ2007 ከነበረው በ 11.3 % ብልጫ ያለው ነው። በየፕሮግራሙ እና በድምር የተቀመጠው መጠን መጀመርያ ላይ የተፈቀደልን ሲሆን አጠቃቀም ላይ የባጀት ዝውውር ስላደረግን እና ተጨማሪ ባጀት ስለተፈቀደልን እስከ መጋቢት 2008 ድረስ ተስተካክሎ የተፈቀደልን መደበኛ ባጀት የሚከተውን ይመስላል፤

- ለፕሮግራም አንድ (አስተዳደር ስራዎች) 141083440.00
- ለፕሮግራም ሁለት (አካዳሚክ ሰራዎች) 122925076.00
- ለፕሮግራም ሶስት (ምርምር ስራዎች) 5820200.00
- ለፕሮግራም አራት (ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች) 2253000.00
- የመደበኛ ባጀት ድምር **272081716.00**

ከታች በሚገኙት ሰንጠረገሮች ተጠቃሎ እንደተመለከተው እስከ መጋቢት 30/2008 የነበረው የመደበኛ ባጀት አጠቃቀም ለኣመቱ ተስተካክሎ ከተፈቀደልን መጠን ጋር ሲነፃፀር 70% ስለሆነ አፈፃፀሙ ጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ መሆኑ ማስቀመጥ ይቻላል።

መደበኛ ባጀቱ የሚመደበው ለደምወዝ፤ ለእቃዎችና አገልግሎት ግዥዎች እና ለሌሎች ተመሳሳይ ወጪዎች ሲሆን ግዥዎችን በተመለከተ በርካታ የግልፅ ጨረታዎች እንዲሁም በውሱን ጨረታ፤ በፕሮፎርማ፤ በለቀማ እና በቀጥታ ግዥዎች በመጠቀም የተለያዩ ግዥዎች ተከናውነዋል። በ2008 ከአምስት ሺ በላይ አዲስ መደበኛ ተማሪዎችን ለመቀበል በያዝነው እቅድ መሰረት ለነዚህ ተማሪዎች የሚሆኑ የተለያዩ ማቴርያሎች ማለትም አልጋ፤ ወንበር፤ ፍራሽ፤ ሎከር፤ ወዘተ እንዲሁም አዲስ ለተቀጠሩና ለነባር ሰራተኞች የሚሆኑ ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ወንበሮች፤ ጠረጴዛዎች፤ እና ሌሎች ማቴርያሎች፤ በተጨማሪም ለማስተማርያ እና ቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶች (ወረቀት፤ መፃህፍት ወዘተ)፤ ለተማሪዎች ምግብ ቤት አገልግሎት የሚውሉ የምግብ ግብአቶች እና መሳርያዎች ግዥዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል።

በዘጠኝ ወራት የነበረው የባጀት አጠቃቀም በሚከተሉት ሰንጠረዦች ጠቅለል ብሎ የቀረበ ሲሆን ከላይ እንደተቀመጠው የመደበኛ ባጀት አጠቃቀም 70% የደረሰ መሆኑን ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 14፤ የመደበኛ ባጀት ኣጠቃቀም በባጀት መደብ (እስከ መጋቢት 30/2008)

| የባጀት መደብ | መጀመርያ የተፈቀደ | ተስተካክሎ የተፈቀደ | እስከ መጋቢት 30 ወጪ የተደረገ | አጠቃቀም በመቶኛ (ተስተካክሎ የተፈቀደውን በመጠቀም) |
|---|---|---|---|---|
| 6100 | 104504900.00 | 115092176.00 | 87919424.83 | 76.39 |
| 6200 | 123519740.00 | 131954740.00 | 85168383.37 | 64.54 |
| 6300 | 22234800.00 | 21899800.00 | 13891770.11 | 63.43 |
| 6400 | 3135000.00 | 3135000.00 | 3176097.90 | 101.31 |
| **ድምር** | 253394440.00 | 272081716.00 | 190155676.21 | 69.89 |

ሰንጠረዥ 15፤ የመደበኛ ባጀት ኣጠቃቀም በፕሮግራም (እስከ መጋቢት 30/2008)

| ፕሮግራም | ተስተካክሎ የተፈቀደ | እስከ መጋቢት 30 የተጠቀምንበት | አጠቃቀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| ፕሮግራም አንድ (392-01-01-00): አስተዳደር | 141083440 | 102846795.5 | 72.90 |
| ፕሮግራም ሁለት (392-02-01-00): አካዳሚ | 122925076 | 85918046 | 69.89 |
| ፕሮግራም ሶስት (392-03-01-00): ምርምር | 5820200 | 852833.53 | 14.65 |
| ፕሮግራም አራት (392-04-01-00): ማህበረሰብ አገልግሎት | 2253000 | 538001.21 | 23.88 |
| ድምር | 272081716 | 190155676.2 | 69.89 |

## 3.2. ካፒታል ባጀት

ለካፒታል ባጀት ስራዎች ለ2008 የተፈቀደልን ባጀት ልክ እንደ መደበኛው ሁሉ በፕሮግራም ባጀት መልክ ለስድስት ፕሮግራሞች የተመደበ ነው። በዚሁም መሰረት መጀመርያ የተፈቀደልን የካፒታል ባጀት የሚከተለውን ይመስላል፤ ለፕሮግራም አንድ 179299600.00፤ ለፕሮግራም ሁለት 4896850.00፤ ለፕሮግራም ሶስት 20676000.00፤ ለፕሮግራም አራት 29905550.00፤ ለፕሮግራም አምስት 26190000.00 እና ለፕሮግራም ስድስት 44960000.00 በአጠቃላይ የተፈቀደልን የካፒታል ባጀት 350000000.00 ነው። በ2007

መጀመርያ ላይ ተፈቅዶልን ከነበረው የብር 334155920.00 ባጀት ጋር ሲነፃፀር የ2008 ባጀት የ15844080.00 ወይም የ4.74% ብልጫ ያለው ነው። በሂደት የባጀት ዝውውር በማድረግና ተጨማሪ ባጀት በመጠየቅ በየፕሮግራሙ ተስተካክሎ የተፈቀደልን ባጀት የሚከተለውን ይመስላል፤

- ለፕሮግራም አንድ 246022850.00
- ለፕሮግራም ሁለት 166549601.00
- ለፕሮግራም ሶስት 20676000.00
- ለፕሮግራም አራት 23905550.00
- ለፕሮግራም አምስት 16190000.00
- ለፕሮግራም ስድስት 23656000.00
- ድምር **497000001.00**

እስከ ታህሳስ 2008 የነበረው የስድስት ወራት የባጀት አጠቃቀሙ እንደሚያሳየው 80% የደረሰ ሲሆን በስድስት ወር አፈፃፀም ሪፖርት ተገልፆ እንደነበረው የካፒታል እጥረት ስላጋጠመን የባጀት ማስተካከያዎችን ያደረግን ሲሆን እንዲሁም ተጨማሪ ባጀት ጠይቀን ተፈቅዶልናል። በየሂሳብ መደቡ እና በየፕሮግራሙ የነበረው አፈፃፀም በሚከተሉት ሁለት ሰንጠረዦች ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 16፤ የካፒታል ባጀት አጠቃቀም በባጀት መደብ (እስከ መጋቢት 30/2008)

| የሂሳብ መደብ | መጀመርያ የተፈቀደ | ተስተካክሎ የተፈቀደ | እስከ መጋቢት 30 ጥቅም ላይ የዋለ | አጠቃቀም በፐርሰንት (ተስተካክሎ የተፈቀደ በመጠቀም) |
|---|---|---|---|---|
| 6100 | 19565000.00 | 19565000.00 | 14026548.04 | 71.69 |
| 6200 | 9575500.00 | 13575500.00 | 6616755.68 | 48.74 |
| 6300 | 320859500.00 | 463859501.00 | 376394771.45 | 81.14 |
| 6400 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | |
| **ድምር** | 350000000 | **497000001** | **397038075.2** | **79.89** |

ሰንጠረዥ 17፤ የካፒታል ባጀት አጠቃቀም በፕሮግራም (እስከ መጋቢተ 30/2008)

| ፕሮግራም | ተስተካክሎ የተፈቀደ | እስከ መጋቢት 30 የተከፈለ | አጠቃቀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| ፕሮግራም አንድ (392-01-01-010-001) | 246022850.00 | 201844631.75 | 82.04 |
| ፕሮግራም ሁለት (392-01-01-010-002) | 166549601.00 | 133288701.17 | 80.03 |
| ፕሮግራም ሶስት (392-01-01-010-003) | 20676000.00 | 15721633.17 | 76.04 |
| ፕሮግራም አራት (392-01-01-010-004) | 23905550.00 | 18383430.25 | 76.90 |
| ፕሮግራም አምስት (392-01-01-010-005) | 16190000 | 10903026.36 | 67.34 |
| ፕሮግራም ስድስት (392-01-01-010-006) | 23656000 | 16896652.47 | 71.43 |
| **ድምር** | **497000001.00** | **397038075.17** | 79.89 |

## 4. የግንባታ ስራዎችን አፈፃፀም

በአመቱ እቅድ በዝርዝር እንደተቀመጠው በ2008 በርካታ የግንባታ ስራዎችን ለማከናወን ፕላን ተይዟል። በእቅዱ መሰረት በ2007 የተጀመሩት የግንባታ ስራዎች የቀጠሉ ሲሆን በ2008 የሚጀመሩ አዳዲስ ስራዎች እንደሚኖሩ ተደርጎ ተቀምጧል።

በዚሁም መሰረት ቀደም ብለው ተጀምረው የነበሩት የግንባታ ስራዎች እና የዘጠኝ ወር አፈፃፀማቸው የሚከተለውን ይመስላል፤

- በዋናው ግቢ ቀደም ብለው የተጀመሩት የአራተኛው ዙር 23 ብሎኮች ግንባታ (በ14 ኮንትራክተሮች የተሰሩ) አፈፃፀማቸው በሙሉ ተጠናቀው (100%) ስራ ላይ ውለዋል (ዝርዝር አፈፃፀሙ በAppendix 2 ማየት ይቻላል)። ከነዚህ በተጨማሪም ከአራተኛው ዙር ብሎኮች ዘግይቶ የተጀመረው እና በዋናው ግቢ በመገንባት ላይ ያለው ሁለተኛው ማእከላዊ ላይብረሪ (Centeral Library) ስራው የተጠናቀቀ ሲሆን አገልግሎት በቅርቡ እንደሚጀምር ይጠበቃል።

- በሁለተኛው ግቢ ከሰኔ 2007 ጀምሮ በመገንባት ላይ ያሉት 32 ብሎኮች አማካይ የአፈፃፀም ደረጃቸው 88.78 ላይ ይገኛል፤ የየብሎኩ የአፈፃፀም ዝርዝር በAppendix 3 በሚገኘው ሰንጠረዥ ተመልክቷል።

- የዋናው ግቢ አጥር ግንባታ ስራዎች በተመለከተ ያለው አፈፃፀም ስራው የተጠናቀቀ መሆኑን ያሳያል፤ ዝርዝሩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ማየት ይቻላል።

ሰንጠረዥ18. የዋናው ግቢ አጥር ግንባታ አፈፃፀም

| S. No. | Name of Contractor | Typology | Contract Amount | Vat | Contract Amount with Vat | Executed % | Executed Amount |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Hailemariam Hiluf B.C | C1 | 13,451,328.93 | 2,017,699.34 | 15,469,028.27 | 100.00 | 13,451,328.93 |
| 2 | Nigus Aynimishet B.C | C2 | 11,199,713.21 | 1,679,956.98 | 12,879,670.19 | 100.00 | 11,199,713.21 |
| 3 | Welday Hailu B.C | C3 | 10,906,482.92 | 1,635,972.44 | 12,542,455.36 | 100.00 | 10,906,482.92 |
| አማካይ | | | 35,557,525.06 | 5,333,628.76 | 40,891,153.82 | **100.00** | 35,557,525.06 |

- የመሰረት ልማት እና የፍሳሽ ማጣርያ ግንባታ አፈፃፀም የመሰረተ ልማቱ (ሁለተኛው ዙር መሰረተ ልማት) 95% የደረሰ ሲሆን የፍሳሽ ማጣርያ ፕላንት (Waste Water Treatment Plant) አፈፃፀም ደግሞ 55% ደረጃ ላይ ይገኛል። የሁለቱም ዝርዝር አፈፃፀም በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 19. የመሰረተ ልማት (ሁለተኛ ዙር) እና የፍሳሽ ማጣርያ ግንባታ አፈፃፀም

| Name of Contractor | | Typology | Contract Amount | | Executed % |
|---|---|---|---|---|---|
| United Construction P.L.C | Phase II | Infrastructure | 45,519,373.15 | 52,347,279.12 | 95.00 |
| United Construction P.L.C | | treatment plant | 161,837,506.09 | 89,010,628.35 | 55.00% |

- ለመምህራን መኖርያ ተብለው ከክልሉ የቤቶች ልማት ኤጀንሲ የተገዙት ያላለቁ 12 የኮንዶሚንየም ብሎኮች የግንባታ ስራዎችን ኣፈፃፀም በሚከተለው ሰንጠረዥ በዝርዝር እንደሚታየው የግንባታ ስራው ተጠናቋል። ከአስራ ሁለቱ ብሎኮች ዘጠኙ በዋናው ግቢ አጠገብ የሚገኙ ሲሆን ሶስቱ ደግሞ በሁለተኛው ግቢ አጠገብ የሚገኙ ናቸው። የቤቶቹ ግንባታ የተጠናቀቀ ቢሆንም የውሃ ማጨራቀምያ ገንዳዎች እና የፍሳሽ ማጠራቀምያ ሴፐቲክ ታንኮች መሰራት ስላለባቸው እንዚህን ለመስራት ጨረታ ስልወጣ የግንባታው ስራ በቅርቡ የሚጀመር ይሆናል። እነዚህ ስራዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ቤቶቹ በተሟላ ሁኔታ ለአገልግሎት ዝግጁ ስለሚሆኑ መመርያ ወጥቶለት ቤቶቹን ለመምህራን የማከራየት ስራ የሚቀጥል ይሆናል።

ሰንጠረዥ 20፤ የመምህራን መኖርያ ኮንደሚንየም ቤቶች ግንባታ ኣፈፃፀም

| Name of Contractor | Typology | Contract Amount | Vat | Contract Amount with Vat | Executed % | Executed Amount |
|---|---|---|---|---|---|---|
| NUGUS BERHE RC&BC LOT-1 | T4-1 G+3 | 2,381,851.62 | 357,277.74 | 2,739,129.36 | 100.00 | 2,381,851.62 |
| | T4-2 G+3 | 2,296,278.61 | 344,441.79 | 2,640,720.40 | 100.00 | 2,296,278.61 |
| | T3- G+3 | 3,738,312.11 | 560,746.82 | 4,299,058.93 | 100.00 | 3,738,312.11 |
| ABEBE TUKE BC-LOT-4 | M1 G+3 | 3,087,312.08 | 463,096.81 | 3,550,408.89 | 100.00 | 3,087,312.08 |
| | M2 G+3 | 2,824,905.65 | 423,735.85 | 3,248,641.50 | 100.00 | 2,824,905.65 |
| NUGUS AYNIMSHET BC -LOT-5 | M1 G+3 | 3,974,269.86 | 596,140.48 | 4,570,410.34 | 100.00 | 3,974,269.86 |
| | T4 G+3 | 3,315,633.93 | 497,345.09 | 3,812,979.02 | 100.00 | 3,315,633.93 |
| TEKLAY TAFERE BC - LOT-3 | M1 G+3 | 3,400,660.84 | 510,099.13 | 3,910,759.97 | 100.00 | 3,400,660.84 |
| | M2 G+3 | 2,592,177.08 | 388,826.56 | 2,981,003.64 | 100.00 | 2,592,177.08 |
| TSIGABU G/SILASE GC - LOT-2 | BL G+3 | 2,938,059.60 | 440,708.94 | 3,378,768.54 | 100.00 | 2,938,059.60 |
| | M2 G+3 | 3,489,619.25 | 523,442.89 | 4,013,062.14 | 100.00 | 3,489,619.25 |
| | T4 G+3 | 2,602,865.13 | 390,429.77 | 2,993,294.90 | 100.00 | 2,602,865.13 |
| **አማካይ** | | **36,641,945.76** | **5,496,291.86** | **42,138,237.62** | **100.00** | **36,641,945.76** |

በ2008 ኣዲስ ይሰራሉ ተብለው የታቀዱት የግንባታ ስራዎች እና ያላቸው ኣፈፃፀም ደረጃ ደግሞ በሚከተለው መልኩ የቀረበውን ይመስላል።

- ተጨማሪ አምስት ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ማስቆፈር፤ ለዚሁ ስራ ይሆን ዘንድ ጨረታ ወጥቶ ኣሸናፊው ተለይቶ የቁፋሮው ስራ የተጀመረ ሲሆን እስካሁን ድረስ ሁለት ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ተቆፍረው ለጥቅም ዝግጁ የሆኑ ሲሆን ሶስተኛው ጉድጓድ ደግሞ በመቆፈር ላይ ይገኛል። የሚቀሩት የሁለት ጉድጓዶች ለመቆፈር የቦታ መረጣ ስራ የተከናወነ ሲሆን በተመረጡ ቦታዎች ላይ ከኣከባቢው ኣስተዳደር እና ነዋሪዎች ጋር ከካሳ ክፍያ እና ቦታውን ለተመረጠው ስራ ከመፍቀድ (ከክልሉ የውሃ ሃብት ቢሮ ደግሞ

ፈቃድ ስለሚያስፈልግ) ጋር ተያይዘው የሚታዩ ችግሮች የስራ መዘግየት መፍጠራቸው ግን አልቀረም።

- አዲስ የተቆፈሩትን እና ቀደም ብለው ተቆፍረው የነበሩት ነገር ግን ወደ ግቢው (ዋናው ግቢ) ከሚገባው መስመር ጋር ያልተያያዙትን ለማያያዝ ይረዳ ዘንድ የማከማቻ ገንዳ (Collection Chamber) እና የመስመር ዝርጋታ ስራዎችን የመስራቱ ጉዳይ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊው ተለይቶ የማከማቻ ገንዳው እና የመስመር ዝርጋታ ስራዎች በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል። ሰራው ካለቀ በኋላ በዋናው ግቢ ያጋጠመው ከፍተኛ የውሃ እጥረት እንደሚፈታ ይጠበቃል። በአመቱ መጨረሻ ላይ እንደሚደርስ የሚጠበቅ ቢሆንም ዞሮ ዞሮ ለሚቀጥለው የትምህርት ዘመን ነው ጠቀሜታ ሊኖረው የሚችለው። ስለዚህ እስካሁን እየተሰራበት ያለው ጊዚያዊ መፍትሄ (ማለትም በቦቴ ውሃ የማመላለስና በግቢው ውስጥ በተተከሉት የውሃ ገንዳዎች አመካኝነት እየተደረገ ያለው ውሃ የማቅረብ ስራ) የሚቀጥል ይሆናል።
- የማኔጅመንት ህንፃ ዲዛይን በማጠናቀቅ የግንባታ ስራ መጀመር፤ የማነጅመነት ህንፃ ዲዛይን በጨረታ ለማሰራት እና ኣብሮ የግንባታ ስራ ጨረታ ለማውጣት የሚያስችል ሰነድ ተዘጋጅቶ ጨረታ የወጣ ሲሆን አሸናፊውን ለመለየት የትንተና ስራ በመሰራት ላይ ነው። ኣሸናፊው ከተለየ በኋላ ስራው የሚጀመር ይሆናል።
- በከተማው ሆስፒታል ለዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች (የህክምናና ጤና ሳይንስ) እንዲሁም ለሆስፒታሉ ኣገልግሎት የሚውል ብሎክ ማሰራት፤ ብሎኩን ለማስራት የዲዛይን ክለሳ ተደርጎ ጨረታ ወጥቶ ኣሸናፊው ለመለየት ተለይቶ በግዥ አፅዳቂ እንዲፀድቅ ተደርጓል። ከክልሉ የጤና ቢሮ እና ከሆስፒታሉ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ከተፈረመ በኋላ የግንባታው ስራ የሚጀመር ይሆናል።
- ከትግራይ ልማት ማህበር ጋር በመተባበር በከተማው የሚሰራው ሞዴል ትምህርት (Community School) ቤት ግንባታ በተመለከተ የከተማው ኣስተዳደር ለስራው የሚሆን ሳይት ፕላን ስላላቀረበ ስራው ኣልተጀመረም።
- በዩኒቨርሲቲው ያለው የመመረቅያ ኣዳራሽ ተስማሚ ወንበር የመግጠምና የኤሌክትሮ ሜካኒካል ተከላዎችን ለማካሄድ የሚየሰችሉ ሁለት ጨረታዎች ወጥተው ኣሸናፊዎች ተለይተው ስራው ተጠናቆ ለአገልግሎት ዝግጁ ሆኗል።
- የግቢው ላንድስኬፕ ስራ በተመለከተ ለጨረታ የሚሆን ሰነድ በመዘጋጀት ላይ ስለሚገኝ ሰነዱ እንዳለቀ ጨረታ የሚወጣ ይሆናል።
- የማስተማርያ ሆስፒታል በሁለተኛው ግቢ ለመገንባት የሚያስችል የዲዛይን ስራ ለመስራት የታቀደው እቅድ በተመለከተ የዲዛይን ስራው በመንግስት የዲዛይን ስራዎች ባለስልጣን እንዲሰራልን ጥያቄ ለማቅረብ በዝግጅት ላይ እንገኛለን።

## 5. የእቅድ ኣፈፃፀም

ዩኒቨርሲቲው ስራ ከጀመረበት ከ2004 ጀምሮ በቁልፍ ተግባር ዙርያ አመታዊ ዝርዝር እቅድ በማዘጋጀትና በእቅዱ ላይ መግባባት በመድረስ ነው የዓመቱ  ስራዎች ትግበራ የሚጀመረው። በየአመቱ ደግሞ መሪ ቃል (motto) እየተዘጋጀ በዚሁ መሪ ቃል በመሰባሰብ የአመቱን እቅድ በመፈፀም እና የእቅድ አፈፃፀምም በስድስት ወር እና በአመቱ መጨረሻ ጠቅላላው የዩኒቨርሲቲ መምህራን እና ሰራተኞች በሚገኙበት መድረክ እንዲገመገም ይደረጋል። ለምሳሌ ዩኒቨርሲቲው ሰራውን በ2004 ሲጀምር የነበረው መሪ ቃል " ነባር ዩኒቨርሲቲዎች ከደረሱበት ደረጃ ተነስተን ወደፊት እንጓዝ" የሚል ነበር።

በተመሳሳይ መልኩ የዩኒቨርሲቲው የ2008 ቁልፍ ተግባር ተደርጎ የተለየው **"በአግባቡ የተደራጀ የትምህርት ልማት ሰራዊት በመጠቀም መልካም አስተዳደር፤ ሰላማዊ መማር ማስተማር፤ እና የትምህርት ጥራት የሰፈነበት ዩኒቨርሲቲ እንዲሆን ማድረግ"** የሚል ሲሆን በዚሁም የአመቱ ዋናው ተግባር የልማት ሰራዊትን በመጠቀም የዩኒቨርሲቲውን አላማዎች ለማሳካት ከፍተኛ ጥረትን ማድረግ የሚያመለክት ነው። ቁልፍ ተግባሩን መሰረት በማድረግ ደግሞ በየአመቱ እንደሚደረገው ለ2008 "**ለትምህርት ጥራት ሙሉ ቁመና ያለው የትምህርት ልማት ሰራዊት**" የዩኒቨርስቲው መሪ ቃል (motto) ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል። የኣመቱ ቁልፍ ተግባር እና መሪ ቃል ዩኒቨርሲቲው በ2008 ለማከናወን ያቀዳቸው ተግባራት ማሳካት የሚቻለው ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች እንደየክፍሉ ሁኔታ የተመደበላቸውን ስራ በሚገባ ሲያከናውኑ ከዚሁም አልፎ ደግሞ ሁሉም ክፍሎች እየተባበሩና እየተጋገዙ እንደ አንድ አሃድ ሆነው የዩኒቨርሲቲውን ሶስት ተልእኮዎች ማሳካት ሲችሉ መሆኑን ያሳያሉ። ይሄንን ማሳካት የሚቻለው ደግሞ የተጠናከረ እና የሚናበብ የልማት ሰራዊት ሲኖር እንደሆነ የሚያመለክት ነው።

በዚሁም መሰረት የ2007 ስራ አፈፃፀም ሓምሌ 10/2007 ጠቅላላ መምህራንና ሰራተኞች ባሳተፈ መልኩ ከተገመገመ በኋላ የ2008 ዝርዝር እቅድ ተዘጋጅቶ እና በዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ቦርድ ፀድቆ አስፈላጊው የዝግጅት ስራዎች ከተሰሩ በኋላ የትግበራ ምእራፍ ስራዎችም በተያዘው እቅድ መሰረት በመከናወን ላይ ናቸው። የስድስት ወረ የአፈፃፀም ግምገማ የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞች እንዲሁም የዩኒቨርሰቲው አስተዳደር ቦርድ ሰብሳቢ በተገኙበት የካቲት 25/2008 ተካሂዷል። ዝርዝር የአፈፃፀም ሁኔታው ነጥብ በነጥብ በሰንጠረዥ መልክ የቀረበ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 5.1. የቁልፍ ተግባር አፈፃፀም

ዩኒቨርሲቲው እስካሁን በጥሩ ሁኔታ ከሰራቸው ነገሮች ኣንዱ የትምህርት ልማት ሰራዊት ግንባታና ኣፈፃፀም ነው። ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ በ2007 የመጀመርያ ደረጃ የልማት ሰራዊት መገንባት የቻለ ሲሆን የተፈጠረው የልማት ሰራዊት በ2008 ደግሞ ተጠናክሮና ሙሉ ቁመና ይዞ እንዲወጣ በእቅድ ያስቀመጠው ቁልፍ ተግባር ነው። በዚሁም መሰረት ቀደም ብሎ የተጀመረውን ስራ በማጠናከር ዘንድሮም የቀጠለበት ሲሆን በርካታ የኣንድ ለኣምስት ኔትወርኮችና የልማት ቡድኖች በሁሉም የዩኒቨርሲቲው ኣካላት (በኣካደሚክ ክንፉ እና በኣስተዳደር ክንፉ እንዲሁም በተማሪው ማህበረሰብ) ተቋቁመው የሚጠበቅባቸውን ተግባራት በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

በዚሁም መሰረት በስድስቱ ኮሌጆች እና 40ዎቹ የትምህርት ክፍሎች (Appendix 4 ይመልከቱ) ተቋቁመው በስራ ላይ የሚገኙት የተማሪዎችና የመምህራን የኣንድ ለኣምስት ኔትወርኮችና የልማት ቡድኖች በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ የተቀመጠውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 21፤ በየኮሌጁ የሚገኙ የተማሪዎችና የመምህራን የአንድ ለአምስት ኔትዎርኮችና የልማት ቡድኖች ማጠቃለያ

| ኮሌጅ | ተማሪዎች | | መምህራን | |
|---|---|---|---|---|
| | 1 ለ 5 ኔትወርክ | ልማት ቡድን | 1 ለ 5 ኔትወርክ | ልማት ቡድን |
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ | 1150 | 123 | 44 | 8 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 233 | 28 | 23 | 8 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | 234 | 22 | 12 | 6 |
| ግብርናና አከባቢ ሳይንስ | 173 | 16 | 8 | 5 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 350 | 42 | 12 | 4 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ | 216 | 29 | 18 | 10 |
| ድምር | 2356 | 260 | 117 | 41 |

በሰንጠረዡ እንደሚታየው በዩኒቨርሲቲው በጠቅላላ 2356 የተማሪዎች የአንድ ለአምስት መረቦች (Cooperative Learning) የሚገኙ ሲሆን የልማት ቡድኖች ቁጥር ደግሞ 260 ነው። ተማሪዎች በአንድ ለአምስት በሚደራጁበት ጊዜ መጀመርያ ተገቢውን ኦርየንቴሽን ለነባርም ሆነ ለአዲስ ተማሪዎች በመስጠት ያሉዋቸውን ጥያቄዎች ሆኑ ጥርጣሬዎች እንዲያነሱ በማድረግ እና ያሉንን አደረጃጀቶች በመጠቀም ነባር ተማሪዎች ያገኙትን ጠቀሜታ እንዲያብራሩ በማድረግ መግባባት ላይ ተደርሶ አደረጃጀቱ በማጠናከር በዩኒቨርስቲው የትምህርት ልማት ሰራዊት ግንባታ መልካም የሚባሉ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። መግባባቱ ከተፈጠረ በኋላ ነባር ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ባላቸው ውጤት (አዲስ ተማሪዎች ደግሞ ባላቸው የ12ኛ መልቀቅያ ፈተና ውጤት) መሰረት የተሻለ ውጤት ያላቸው እና ደከም ያለ ውጤት ያላቸው እንዲሁም ሁኔታዎች እስከፈቀዱ ወይም ተሟልተው እስከተገኙ በቋንቋ፤ በሃይማኖት፤ በፆታ ወዘተ በማሰባጠር ወይም በሚያመጣጥን መልኩ እንዲደራጁ በማድረግ ነው የሚተገበረው። ይህም ማለት በየክፍሉ ያሉት ተማሪዎች ሁኔታ መሰረት በማድረግ ከተለያዩ ክልሎች የመጡ እንዲኖሩበትና በፆታና የሃይማኖት ስብጥርም ያካተተ እንዲሆን ይደረጋል ማለት ነው። በተለይ አዲስ የኢንጂነሪንግ ተማሪዎች አንደኛ ሰሚስተር ላይ በትምህርት ክፍል ሳይሆን በጋራ አንድ ላይ የቅድመ ምህንድስና (Pre-engineering) ትምህርት ስለሚማሩ ሁለተኛ ሰሚስተር ላይ ወደየትምህርት ክፍሉ ስለሚመደቡ እንደ አዲስ ውጤታቸውን መሰረት ባደረገ መልኩ ወደ አንድ ለአምስት ቡድኖች እንዲመደቡ ይደረጋል።

ተማሪዎች በዚህ መልኩ ከ5-7 እየሆኑ በአንድ ቡድን ሲደራጁ በየክፍሉ (Section) ደግሞ የልማት ቡድን ይኖራቸዋል። እያንዳንዱ ቡድንና በቡድኑ ያሉት ተማሪዎች እያንዳንዳቸው በየሰሚስተሩ እቅድ (እያንዳንዱ ተማሪ ለእያንዳንዱ ኮርስ ሊያገኘው የሚያቅደው ውጤት) የሚያዘጋጁ ሲሆን በየሳምንቱ መጨረሻም አጠር ያለና በዩኒቨርሰቲው የተዘጋጀ ቅፅ በመሙላት ሪፖርት ለልማት ቡድናቸውና ለትምህርት ክፍል ሃላፊያቸው ያቀርባሉ። በየደረጃው ያሉ ሃላፊዎችና የየክፍሉ ሜንተሮች (መምህራን) አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ስለሚያደርጉላቸው የተማሪዎች እርስ በርስ መደጋገፉ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል። ከላይ እንደተጠቀሰው የተማሪ አንድ ለአምስት ቡድኖች (Cooperative Learning Teams) የተዘጋጀላቸውን ፎርማት በመጠቀም እቅድና ግብ (ታርጌት) የሚያዘጋጁ ሲሆን በየሳምንቱ መቼና በስንት ሰአት እንደሚገናኙ ፕሮግራም ይይዛሉ። የሰሩትን ስራ በተመለከተ ደግሞ ሪፖርት ያቀርባሉ። የሚገናኙበት ፕሮግራም እና የሚገናኙበት ቦታ በትምህርት ክፍላቸው የሚታወቅ ሆኖ በነዚህ ቀናት በሜንተርነት የተመደቡ መምህራን ክትትል ያደርጉላቸዋል። ሌሎች የየትምህርት አይነቱ መምህራንም ተማሪዎቹ በቡድን ውይይት ወቅት ለሚያነሱዋቸው ጥያቄዎች በማስረዳት ይሳተፋሉ። በየፕሮግራሙ መሰረት መምህራን ከስራ ሰአታት ውጭም

ጭምር እየተገኙ (ለምሳሌ ምሽት) ድጋፍ ይሰጣሉ። የአንድ ለአምስት ቡድኖች በዩኒቨርሲቲው ላይብረሪ (ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ቦታ) እና በመማርያ ክፍሎችና አደራሾች እየተገናኙ ነው እርስ በርስ የሚደጋገፉት። ላይብረሪው የሃያ አራት ሰአት አገልግሎት ስለሚሰጥ በላይብረሪው ውስጥ የሚገኘው የተማሪዎች አንድ ለአምስት መወያያ አዳራሽም (Network Halls) እንዲሁ የሃያ አራት አገልግሎት ይሰጣል። በድምሩ ሲታይ በሚፈለግበት ደረጃ ላይ የደረሰ ነው ባይባልም የተማሪዎች የልማት ሰራዊት ግንባታ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ነው ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል።

ከተማሪዎች በተጨማሪ በመምህራን አከባቢ ደግሞ በየትምህርት ክፍሉና በየኮሌጁ በድምሩ 117 የአንድ ለአምስት መረቦችና 41 የልማት ቡድኖች ተቋቁመዋል። እያንዳንዱ ትምህርት ክፍል አንድ የልማት ቡድን የሚኖረው ሲሆን የልማት ቡድኑ አስተባባሪ ደግሞ የትምህርት ክፍሉ ሃላፊ ነው። በዚህም መሰረት 40 ተማሪዎችን የሚቀበሉና 1 ተማሪዎችን የማይቀበል የትምህርት ክፍል (Department of Biomedical Sciences) ስላሉን የመምህራን የልማት ቡድኖች 41 ሊሆኑ ችለዋል። የመምህራን የአንድ ለአምስት መረቦች ከተማሪዎች መረቦች ጋር ተናበውና ተደጋግፈው እንዲሰሩ ማድረግ ዘንድሮ የተያዘ አቅጣጫ ሲሆን የመምህራን የልማት ሰራዊት ግንባታ ከአምና በተሻለ መልኩ እየሰሩበት የሚገኝ ቢሆንም ከተማሪዎች ጋር ሲነፃፀር እና ሊደረስበት ከሚፈለገው ደረጃ ጋር ሲወዳደር ገና ብዙ የሚቀረው ስራ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል። በድጋፍ ሰጪ ክንፎች የተመሰረቱት የአንድ ለአምስት መረቦችና የልማት ቡድኖች ደግሞ በሚከተለው ሰንጠረዥ የተቀመጠውን ይመስላል። አፈፃፀማቸው ግን በተማሪዎች ቡድኖች እንደታየው ጠንካራ ስላልሆነ እንደመምህራኑ ሁሉ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራበት የሚሰራ ቢሆንም ከሌሎች የተሻለ ስራ የሰሩ ደግሞ የቤተ መፃህፍትና የምግብ ቤት ቡድኖች ይገኙበታል።

ሰንጠረዥ 22፤ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የአንድ ለአምስት ኔትዎርኮችና የልማት ቡድኖች በየክፍሉ

| ክፍል/ፅህፈት ቤት | 1 ለ 5 ኔትወርክ | ልማት ቡድን |
|---|---|---|
| የአካዳሚክ ክንፍ ፀሃፊዎች | 6 | 6 |
| ሰውሃብት ልማት | 3 | 1 |
| ላይብረሪ | 20 | 3 |
| መሰረታዊ አገልግሎት | 25 | 3 |
| ረጂስትራር | 5 | 1 |
| ፋይናንስ አስተዳደር | 2 | 1 |
| ተማሪዎች ዲን | 98 | 5 |
| ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ | 2 | 1 |
| ግዥና ንብረት አስተዳደር | 6 | 2 |
| ሌሎች (ፕረዚደንት፡ ም/ፕረዚደንቶች፡ ዳይሬክተሮች፡ ፀሃፊዎች) | 2 | 1 |
| ድምር | 169 | 24 |

## 5.2. የዝግጅት ስልጠናዎች

እቅዶችን ወደ መተግበር ከመገባቱ በፊት በየአመቱ ሰፋፊ የዝግጅት ስልጠናዎች ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ መስጠት የተለመደ ተግባር ነው። በዚሁም መሰረት በ2008 የስራ ዘመን መጀመርያ ላይ ለመምህራን፤ ለአስተዳደር ሰራተኞች፤ እና ለነባርና አዲስ ተማሪዎች

ተለይተው በተቀመጡ አርእስቶች ዙርያ ስልጠና ተሰጥተዋል። ስልጠናው በአገር አቀፍ ደረጃ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የተከናወነ ነበር። ስለ ስልጠናው አስፈላጊነትና አካሄድ በትምህርት ሚኒስቴር ኦርየንቴሽን ተሰጥቶ እንዲሁም ለስልጠናው አስፈላጊ የሆኑ ፅሁፎች በሚመለከታቸው አካላት ተዘጋጅቶ ነው ስልጠናው የተከናወነው። ለስልጠናው የተለዩ ርእሶች የሚከተሉት ነበሩ።

- የአንደኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈፃፀምና የሁለተኛው እድገትና ትራንስፎረሜሽን እቅድ
- የትምህርት ጥራት ማስጠበቅ ስራችንና የባለድርሻዎች ሚና
- በተቋማዊ ለውጥ ትግበራ የእስካሁኑ አፈፃፀም፣ የአመራሩ ሚናና ቀጣይ አቅጣጫዎች
- የዩኒቨርሲቲው የ2007 እቅድ አፈፃፀም ግምገማ
- የዩኒቨርሲቲው የ2008 እቅድ

ከላይ በተጠቀሱት ርእሶች ለመምህራን፣ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችና ተማሪዎች (አዲስ እና ነባር) ስልጠና የተሰጠ ሲሆን ስልጠናው ከፍተኛ ዝግጅት ተደርጎበት እና በየእለቱ እየተገመገመ የተደረገ ስለነበር በተሳትፎውም በአካሄዱም ውጤታማ ነበር። ስልጠናው የተሰጠው በየደረጃው ባሉት ዩኒቨርሲቲ ሃላፊዎች (ማለትም ፕሪዚደንቶች፣ ዲኖች እና ዳይሬክተሮች) ሲሆን የመምህራንና ሰራተኞች አንድ ላይ መስከረም መጀመርያ ላይ፣ የነባር ተማሪዎች መስከረም መጨረሻ ላይ እና የአዲስ ተማሪዎች ጥቅምት መጨረሻ ላይ ተከናውኗል። የመምህራንና ሰራተኞች ስልጠና ለሰባት ቀናት የነባር ተማሪዎች ለአምስት ቀናት እና የአዲስ ተማሪዎች ደግሞ ለአራት ቀናት ነው ስልጠናው የተሰጠው።

ከተደረጉት ስልጠናዎች ውስጥ አንዱን ዘርዘር ባለ መልኩ ለማስቀመጥ ያህል የመምህራንና ሰራተኞች ስልጠና የተከናወነው ከመስከረም 5 እስከ መስከረም 13 **ለሰባት ቀናት** (መስከረም 9 እሁድ ስለነበረና መስከረም 12 ደግሞ የአረፋ በአል ስለነበረ በነዚህ ቀናት ስልጠናው አልተካሄደም) ነበር የተሰጠው። ስልጠናው አገራዊ ጉዳዮች (የአንደኛው ዕትእ አፈፃፀምና የሁለተኛው እትእ) አንስቶ የቀን ተቀን የዩኒቨርሲቲ ስራዎችን በስፋት ያነሳና ውይይት የተደረገበት ስለነበር ህይወት የነበረው እና በርካታ ትምህርት የተወሰደበት ከመሆኑም በላይ ለአመቱ ስራዎች ዝግጅት የነበረው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። የመምህራንና አስተዳደር ሰራተኞች ስልጠና የተሰጠው በዩኒቨርሲቲው ፕረዚደንትና ምክትል ፕረዚደንት ሲሆን ግምገማዊ መልክ የያዘና ዩኒቨርሲቲው ያለውን ጠንካራና ደካማ ጎን ለመፈተሽ ያስቻለው ነበር። የስልጠና ተሳታፊዎች ያላቸውን ጥያቄዎችና አስተያየቶች በግልፅ ያነሱበትና ክርክር ያደረጉበት ስለነበር የሞቀ ውይይት የተደረገበት ግምገማዊ ስልጠና ነበር። በስልጠናው የነበረ የተሳታፊ ብዛትም አጥጋቢ የነበረ ሲሆን ለምሳሌ በስልጠናው ሁለተኛ ቀን (ሓሙስ መስከረም 06/2008) የተገኙት ተሳታፊዎች ብዛት መገኘት ከነበረባቸው ውስጥ 87% ያህል ነበር። በየክፍሉ የተገኙት ተሳታፊዎች ብዛተ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ 23፤ የዝግጅት ስልጠና ተሳታፊዎች (መምህራንና አስተዳደር ሰራተኞች)፣ መስከረም 06/2008

| ተ.ቁ | የስራ ክፍል | መገኘት የነበረበት ተሳታፊ | | | የተገኘ ተሳታፊ | | | የተገኘ % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| 1 | ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ | 128 | 36 | 164 | 112 | 30 | 142 | 86.59 |
| 2 | ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ | 46 | 15 | 61 | 44 | 12 | 56 | 91.80 |
| 3 | ግብርናና አከባቢ ሳይንስ ኮሌጅ | 25 | 7 | 32 | 25 | 6 | 31 | 96.88 |
| 4 | ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ ኮሌጅ | 67 | 24 | 91 | 60 | 19 | 79 | 86.81 |
| 5 | ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ | 78 | 14 | 92 | 73 | 12 | 85 | 92.39 |
| 6 | ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ | 43 | 17 | 60 | 34 | 13 | 47 | 78.33 |
| | የአካዳሚክ ሰራተኞች ድምር | 387 | 113 | 500 | 348 | 92 | 440 | **88.00** |
| 7 | ፋይናንስ እና ሌሎች | 62 | 39 | 101 | 46 | 36 | 82 | 81.19 |
| 8 | ላይብረሪ | 62 | 73 | 135 | 51 | 63 | 114 | 84.44 |
| 9 | ተማሪዎች ዲን | 65 | 209 | 274 | 60 | 186 | 246 | 89.78 |
| 10 | ሰው ሃብት ልማትና ሌሎች | 104 | 47 | 151 | 75 | 50 | 125 | 82.78 |
| | የአስተዳደር ሰራተኞች ድምር | 293 | 368 | 661 | 232 | 335 | 567 | **85.78** |
| | የጠቅላላ ተሳታፊዎች ድምር | 680 | 481 | 1161 | 580 | 427 | 1007 | **86.74** |

## 5.3. የትምህርት አሰጣጥ

ከቅርብ አመታት ወዲህ በስፋት በዩኒቨርሰቲዎች በኩል እየተተገበረ ያለው የማስተማር እና የነጥብ አሰጣጥ ዘዴ ማለትም የተከታታይ ምዘና ስርአት (Continuous Assessment)፤ ቋሚ መስፈርት ያደረገ የነጥብ አሰጣጥ ስርአት (Criterion Referenced Grading)፤ እንዲሁም ሞዱላር የማስተማር ስርአት (Modularized Curriculum) በዩኒቨርሲተያችን ስራ ላይ እየዋለ ነው። የተከታታይ ምዘናን በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው የ60 – 40 አካሄድ ይጠቀማል። ይህም ማለት ከ60 የሚታሰቡ የተለያዩ አጫጭር ፈተናዎችና አሳይንመንቶች እየተሰጡ ቆይተው መጨረሻ ላይ ደግሞ ከ40 የሚታሰብ የመጨረሻ ፈተና (Summative Exam) ይሰጣል። በነዚህ ፈተናዎች የተገኙ ውጤቶች መሰረት በማድረግ ቋሚ መስፈርትን የተከተለ የውጤት አሰጣጥ እንከተላለን። የሞዱላራይዝድ ካሪከለም አተገባበር በተመለከተ ደግሞ በአብዛኛው ትይዩ በሆነው አካሄድ (Parallel) እየተሰራበት ሲሆን በተወሰኑ ኮርሶች ደግሞ የብሎክ (Block) ኮርስ አሰጣጥ እየተተገበረ ይገኛል። የሞዱላራይዝድ ካሪከለም የላቀ ደረጃ ተደርጎ የሚወሰደው ኢንተግሬትድ (Integrated Modularized Curriculum) ገና ተግባር ላይ ያልዋለ ቢሆንም ስለአተገባበሩ ውይይት እየተደረገበት ይገኛል።

የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በተለይም የተከታታይ ምዘና አካሄድ በተመለከተ በየጊዜው በመምህራን በኩል ጥያቄዎች የሚነሱ ሲሆን (ለምሳሌ በዝግጅት ስልጠና ወቅት በኢንጂነሪንግ አከባቢ ተከታታይ ምዘና መተግበር አስቸጋሪ አይሆንም ወይ የሚል ጥያቄ ተነስቶ ነበር) ከዚሁም በተጨማሪ በርካታ አዲስ አስተማሪዎች ስለተቀጠሩ በተለይ አዲስ የተቀጠሩ መምህራንን መሰረት ያደረገ የማስተማር ዘዴ ስልጠና (Induction Training) በዩኒቨርሳቲው አቅም በኦርየንቴሽን መልክ ተሰጥቷል። የመጀመርያ ቀን መጀመርያ ክፍል (First Day First Class) አተገባበር በተመለከተም ተገቢ ክትትል ስለተደረገበት በጥሩ ሁኔታ ተተግብሯል።

## 5.4. ምርምር እና ህብረተሰብ አገልግሎት

የምርምር ፕሮፖዛሎች የማቅረቡ ጥሪ በ2008 ቀደም ብሎ (ማለትም ከክረምት 2007 ጀምሮ) የተለቀቀ ስለነበር በርካታ ማለትም 111 ፕሮፖዛሎች ቀርበው በእርስ በርስ ትችት (Peer Review) ኣሰራር መሰረት በየኮሌጁ ከየትምህርት ክፍሉ በተውጣጡ መራጭ ኮሚቴ አባላት የምዘና ስራ የተደረገ ሲሆን ፕሮፓዛሎቹ በፅሁፍ ከቀረቡ በኋላ ግልፅ መድረክ እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡ ከቀረቡት 111 ፐሮፖዛሎች ውስጥ በመጨረሻ የተመረጡት 60 የምርምር ፕሮፖዛሎች ሲሆኑ የተመደበላቸው ጠቅላላ በጀት ደግሞ 2.9 ሚልዮን ብር ሲሆን የምርምር ስራዎቹ በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ በየኮሌጁ የተመረጡት የምርምር ፕሮፖዛሎች ብዛትና የተመደበው ባጀት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 24፤ በየኮሌጁ የተመረጡ የምርምር ፕሮፖዛሎች ብዛትና የተመደበላቸው ባጀት

| College | No. of Selected Proposals | Approved budget |
|---|---|---|
| CET | 11 | 513670.0 |
| CNCS | 12 | 596374.0 |
| CHMS | 8 | 389521.0 |
| CAES | 8 | 381154.0 |
| CBE | 9 | 450000.0 |
| CSSH | 12 | 590687.5 |
| Total | 60 | 2921406.5 |

የዩኒቨርሲቲው ሶስተኛ ተልእኮ የማህበረሰብ ኣገልግሎት መስጠት ስለሆነ በየአመቱ እንደሚደረገው ዩኒቨርሲቲው በ2008 ዓ/ም የተለያዩ የማህበረሰብ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ባለፉት ዘጠኝ ወራት የተደረጉት ዋና ዋና የማህበረሰብ አገልግሎቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

(1) በክልል ደረጃ በከተማው የሚከበረው የመስቀል በአል በደማቅ ሁኔታ እንዲከበር የሩጫ ውድድር እና የፓነል ውይይት በማዘጋጀት በጥሩ ሁኔታ ተሳትፏል፡

(2) ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመበት ጀምሮ በከተማው ለሚገኘው የእግርኳስ ክለብ (ወልዋሎእግርኳስ ክለብ አሁን ወልዋሉ ዓዲግራት ዩኒቨርሰቲ እግርኳስ ክለብ) የገንዘብ እና የማቴርያል (የስፖርት ትጥቅ፣ ኳሶች) ድጋፍ እያደረገ ቆይቷል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ባደረገለት ድጋፍ በ2007 የውድድር ዘመን ክለቡ ከነበረበት የብሄራዊ ሊግ ምድብ ሁለተኛ ደረጃ ይዞ የጨረሰ ሲሆን ዘንድሮ 32 አገር አቀፍ ቲሞች በሚሳፉበት የሱፐር ሊግ ምድብ ሊገባ ችሏል፡፡ ክለቡ በዚህ ሊግ ጥሩ ተፎካካሪ እንዲሆንና ወደሚቀጥለው የፕሪምየር ሊግ ደረጃ እንዲያድግ የሚያስችለውን የሰው ሃይል፣ የማቴርያልና የፋይናንስ ኣቅም ስለሚያስፈልገው ዩኒቨርሲቲው ከዳር ሆኖ ክለቡን ከመደገፍ ኣልፎ ከከተማው ኣስተዳደር ጋር በመሆን የጋራ ባለቤትነት ሰነድ (MoU) ተፈራርሟል፡፡ ይህም ክለቡ ሁለት የጋራ ባለቤቶች እንዲኖሩት ተደርጎ ዩኒቨርሲቲው ክለቡን በጋራ የማስተዳደር ሃላፊነት ሊይዝ ችሏል፡፡ በዚሁም መሰረት ዩኒቨርሲቲው ለክለቡ የሚሆን ባጀት (የዩኒቨርሲቲው ቦርድ ባፀደቀው መሰረት) መድቦለታል፡፡

(3) በአከባቢው ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሰጠው የበለስ ተክልን የሚያጠቃው ኮችኔል የተባለ በሽታ በተለይ በደቡባዊ የትግራይ አከባቢ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ ሲሆን ችግሩ ወደ ምስራቃዊ ትግራይ ኣንዳንድ ቀበሌዎች ስለገባ ከፍተኛ ችግር ከማስከተሉ በፊት መስፋፋቱ እንዲቆምና እንዲመለስ (reverse) መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁም መሰረት ከክልሉ የግብርናና ገጠር

ልማት ቢሮ እና ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም ከምስራቃዊ ዞን እና ከክልተ ኣውላዕሎ ወረዳ ኣስተዳደር ጋር በመተባበር ችግሩን ለመፍታት የስልጠና እና የመፍትሄ ማፈላለግ ስራዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል። ዩኒቨርሲቲው በክልሉ የግብርና ቢሮ በሚመራው የስቲሪንግ ኮሚቴ (Steering Committee) እና የቴክኒክ ኮሚቴ (Technical Committee) አባል በመሆን የራሱን ሚና እያበረከ ሲሆን ከአስተዳደሩ፣ ከህዝቡ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ችግሩ የሚገታበት ዞን (buffer zone) ተበጅቶለት ከዚሁ እንዳያልፍ ቁሳቁሶችን በማቅረብ ጭምር በመስራት ላይ ይገኛል። በ2008 በዩኒቨርሲቲው የተቋቋመው የበለስ ኢንስቲትዩት ችግሩን ለመግታትና ለመፍታት በሚደረገው ስራ ዩኒቨርሲቲውን በመወከል በመንቀሳሰቅ ላይ ይገኛል። ለዚሁም ስራ የሚሆን ዩኒቨርሲቲው 500000 ብር መድቦ በመስራት ላይ ይገኛል።

(4)በምስራቃዊ ዞን የሚገኙ 15 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች (High Schools) በመምህራን ና ተማሪዎች በየትምህርት ቤቶቻቸው በዞን ደረጃ ለትምህርት ጥራት መሻሻል ባሳዩት የእውቀትና የፈጠራ ችሎታ (School innovation) በተደረገው ውድድር የማበራታቻ ሽልማት ተሰጥተዋል ።

(5)በትግራይ ክልል የምስራቃዊ ዞን የአርኪዮሎጂ ግኝቶችን መሰረት ያደረገ እና ከካናዳ ዩኒቨርሲቲ ስለጉዳዩ ጥናት ከሚያደርጉት ዶ/ር ካትሪን ጋር በመተባበር ኣለምኣቀፍ የኣርክዮሎጂ ኮንፈረንስ ዩኒቨርሲቲው ኣደራጅቶ በርካታ ከአገር ውስጥ እና ከውጭ አገር የተውጣጡ ባለሞያዎች ተሳትፈውበታል።

(6) በትግራይ ክልል ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሂሳብ መምህራን ለተውጣጡ ባለሞያዎች ከኣሜሪካን ኣገር በመጣ ባለሞያ ኣመካኝነት በሂሳብ እና በፔዳጎጂ ዙርያ ስልጠና ተሰጥል።

(7) ዩኒቨርሲቲው በሚገኝበት ዓዲግራት ከተማ ከፍተኛ የመጠጥ ውሃ ችግር ስላለ ለችግሩ ማቃለያ ይሆን ዘንድ ዩኒቨርሲቲው ኣንድ ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ኣስቆፍሮ ለከተማው አስረክቦታል።

(8) ዩኒቨርሲቲው ጀርመን ኣገር ከሚገኘው የትግራይ ልማት ማህበር ጋር በመተባበር በከተማው ለሚገኘው የዓዲግራት ሆስፒታል የሚያገለግሉ የተለያዩ የህክምና ማቴርያሎች የያዙ ኮንተይነሮች አስመጥቶ ለሆስፒታሉ ድጋፍ አድርጎለታል።

(9) በየኣመቱ የሚከበረው የኤችኤይቪ (HIV) እና ኤይድስ (AIDS) ቀን ዩኒቨርሲቲው በሚገኝበት ዓዲግራት ከተማ በደመቀ ሁኔታ እንዲከበር በስርአተ ፆታ አስተባባሪነት ኣስፈላጊው ዝግጅቶች ተደርገውና የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ተሳትፈውበት እንዲከናወን ተደርጓል።

## 5.5 ለሴት ተማሪዎች የተደረገ ድጋፍ

- የኢኮኖሚ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲው ድጋፍ ያደርጋል። የሚደረገው ድጋፍ የገንዘብና የቁሳቁስ ሲሆን የገንዘብ ድጋፉ ከ2007 ጀምሮ በሰሚስተር 200 ብር እንዲሆን ተደርጓል (ቀደም ብሎ የገንዘብ መጠኑ በሰሚስተር 100 ብር ነው የነበረው)። የኢኮኖሚ ችግር አለባቸው ተብለው ለዚሁ ስራ ተብሎ እና በስርአተ ፆታ ፅ/ቤት በሚመራ ኮሚቴ አመካኝነት ለሚለዩ ተማሪዎች ከገንዘቡ በተጨማሪ በማቴርያል መልክ የሚሰጣቸው ሳሙና (የልብስና የገላ)፤ እስክርቢቶ፤ ደብተር ለወንድና ሴት ተማሪዎች የሚሰጥ ሲሆን ከዚሁ በተጨማሪ ለሴት ተማሪዎች ፓንት፤ ቅባትና፤ ሞዴስ በተጨማሪ ይሰጣል። ከነባር ተማሪዎች ውስጥ ለ480 ተማሪዎች (303 ሴቶችና 177 ወንዶች) እንዲሁም ከኣዲስ ተማሪዎች ውስጥ 412 ተማሪዎች (264 ሴቶችና 148 ወንዶች)

በድምሩ ለ892 ተማሪዎች (567 ሴቶችና 325 ወንዶች) የገንዘብና የማቴርያል ድጋፍ ዩኒቨርሲቲው በማድረግ ላይ ይገኛል። በመቶኛ ሲገለፅ ከተጠቃሚዎች ውስጥ 64% ሴት ተማሪዎች ሲሆኑ 36% የሚሆኑት ደግሞ ወንድ ተማሪዎች ናቸው።

- ለ2200 አዲስ ሴት ተማሪዎች የህይወት ክህሎት(life skill) ስልጠና በስርአተ ፆታ ፅ/ቤት አስተባባሪነት አካሂዷል፤ ስልጠናው በዩኒቨርሲቲው መምህራንና ጤና ባለሞያዎች በቅንጅት የተሰጠ ነው።

- የአካዳሚክ ውጤታቸው በጣም ከፍ ያለ መአርግ (ከ3.75 በላይ) ደረጃ ያላቸው 81 ሴት ተማሪዎች ተለይተው በዩኒቨርሲቲው የማበረታቻ የገንዘብ ሽልማት ተሰጥቷቸዋል።
- በትምህርት ክፍል አመዳደብ ለሴት ተማሪዎች ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ተደርጓል። በዚሁም መሰረት 25% የሚሆኑ ቦታዎች ለሴቶች ብቻ ያለውድድር እንዲደርሳቸው ተደርጓል።
- ሴቶችን ማእከል ያደረገ የቱቶርያል ፕሮግራም በየኮሌጁና ትምህርት ክፍሉ እየተሰጠ ይገኛል።
- በየኮሌጁ ካሉት ሴት መምህራን ውስጥ የስርአተ ፆታ ተጠሪ (Gender Focal Person) እንዲኖር በማድረግ እነዚህ ተጠሪዎች ደግሞ የኬሎጁ ካውንስል አባላት እንዲሆኑ በማድረግና ከስርአተ ፆታ ፅ/ቤት ጋር በመገናኘት ክትትሎች ይደረጋሉ።
- ለ62 አካል ጉዳተኞች የመማርያ ክፍልና የካፌ አጠቃቀም እንዲመቻችላቸው ተደርጓል።

## 5.6. ደረጃውን የጠበቀ የዳታ ሰንተር እና የካምፓስ ኔትዎርክ ዝርጋታ

ብቃትና ፍጥነት ያለው የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት ለዩኒቨርሲቲው ስራዎች መሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ከሚኖራቸው ግብኣቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው። ይሄንን ግምት ባስገባ መልኩ ዩኒቨርሲቲው ስራውን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ሲሰራበት የቆየ ጉዳይ ነው። በተለይም ከ2007 የትምህርት አመት ጀምሮ ደረጃውን የጠበቀ ዳታ ሰንተር (Data Center) እንዲኖር በማድረግ ውጤታማና ከዳታ ሰንተሩ ጋር የሚያያዝ የካምፓስ ኔትወርክ ዝርጋታ ለማከናወን የላቀ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። በዚሁም መሰረት ደረጃውን የጠበቀ የዳታ ሰንተር ግንባታ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። ይህ አገልግሎት በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የመምህራን፣ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፣ እና የመላው ተማሪዎች (በቅድመ ምረቃ እና በድህረ ምረቃ በተለያዩ ፕሮግራሞች የሚገኙ ተማሪዎች) ማህበረሰብ ሊያገለግል በሚችል የተዘጋጀ በመሆኑ በአግባቡ ማስተናገድ የሚችል ነው። የኔትወርክ ዝርጋታ በተመለከተ የሰሚናር እና ቤተመፃሕፍት ህንፃዎችን ጨምሮ በጠቅላላ 24 ህንፃዎች በፋይበር ኦፕቲክስ በማገናኘት የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል። ይህ ስራ ደረጃው የጠበቀ እንዲሆን ሶስት ዘመናዊ የማከፋፈያ ክፍሎች (Mini Data Centers) የተተከሉ ሲሆኑ ከነዚህ ሁለቱ በዘመናዊ እቃዎች ተደራጅተው ተገቢ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪም እያንዳንዱ የኔትዎርክ አገልግሎቶች ተገቢ ደህንነት (security) እንዲኖራቸው ተደርጓል።

ዩኒቨርሲቲው የተማሪዎችና የሰራተኞችን ፍላጎት ለሟሟላት የሚያስፈልግ እንዲሁም ከመጪው ግዜ የሚጣጣም Cloud Power IDS2000-M Modular ዳታ ሴንተር ተክሏል። ይህ ዳታ ሴንተር በአንድ ክፍል ሁሉም የሚያስፈልጉ ሲስተሞች ማለትም integrated IT rack cabinets, power supply distribution system, cooling system, management

system, security system and fire suppression system አጣምሮ የያዘ ነው:: የዳታ ሴንተር አጠቃላይ ዲዛይን የሚከተሉትን የሚያካትት ነው።

- የዴታ ሴንተር ማስጌጫ (Data Center Decoration)
  በዴታ ሴንተር ለሚቀመጡ እቃዎች ድህንነት እንደሚመች ተደርጎ የዴታ ሴንተር ማስጌጫን አስመልክቶ Raised Floor, false ceiling እና Wall painting ይገኙበታል።

- የዴታ ሴንተር ፓወር ስርዓት (Data Center power System)
  ዴታ ሴንተሩ የ7/24 አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ የተሰራ ሲሆን የዴታ ሴንተር ፓወር ሲስተም ይሄንን በሚያስችል መልኩ የተደራጀ ነው።

- የዳታ ሴንተር ማቀዥቀዣ ስርዓት (Air Conditioner)
  ዴታ ሴንተር ውስጥ የተተከሉ እቃዎች ድህንነታቸው እንዲጠበቅ ክፍሉ ደረጃው የጠበቀ የአየር ሁኔታ እንዲኖረው የተተከሉ የአየር ሁኔታ መለኪያ መሳርያዎች (Temperature Sensors) በሚሰጡት መረጃ መሰረት የተተከሉ የክፍል ውስጥ የአየር ማቀዥቀዣ መሳርያ (Indoor Air Conditioner) ለክፍሉ ተገቢ ቀዝቃዜ ይሰጣሉ።

- የዴታ ሴንተር የክትትል ስርዓት (IP Surveillance)
  በዴታ ሴንተሩ አስፈላጊ የክትትል ስርዓት (IP Surveillance System) የተተከሉ ሲሆን እነዚህ ካሜራዎች ከኔትዎርክ ቪድዮ መቅጃ (Network Video Recorder) የተገናኙ ናቸው። በዴታ ሴንተር የተተከለው የኔትዎርክ ቪድዮ መቅጃ ሰርቨር 16 TB የመቅዳት አቅም ያለው ሲሆን እስከ 128 ቻነሎችን ያስተናግዳል።

- የዴታ ሴንተር አስተዳደር ስርዓት (Data Center Management System)
  የዴታ ሴንተር የአስተዳደር ስርዓት በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ ዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓት ተገንብቷል። ይህ አስተዳደር ስርዓት Net Eco የሚባል ሲሆን በዴታ ሴንተር የያንዳንዱ እቃዎች አደረጃጀት እና ተደራሽነታቸው የሚጠቅም ነው። በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲ ያሉ የኔትዎርክ እቃዎች ሁኔታ የሚረጋገጥበት የኔትዎርክ አስተዳደር ስርዓት esight የያዘ ነው። በአጠቃላይ በዩኒቨርስታችን የተገነባው የአይሲቲ መሰረተ ልማት በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ ዘመኑ የሚፈልገው ዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓት ተገንብቶ ስራ ላይ ይገኛል።

- የእሳት መከላለከያ ስርዓት (Fire Suppression System)
  በዴታ ሴንተር የተተከሉ እቃዎች ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር ደህንነታቸው በመጠበቅ የአገልግሎት ዘመናቸው ማራዘም ተገቢ ነው። በዚህ መሰረትም ዘመናዊ የእሳት መከላከያ ስርዓት 120 ኪ.ግ መጠን ያለው (FM 200) የተከለከለ ሲሆን ይህ እቃ በዴታ ሴንተር የተተከሉ የእሳት መኖሩ መቆጣጠርያ መሳርያዎች (Fire Sensors)፣የጭስ መኖሩ የመቆጣጠርያ መሳርያዎች (Smoke sensors) እና ሙቀት መኖሩ የመቆጣጠርያ መሳርያዎች ( Temperature Sensors) በሚሰጡት መረጃ መሰረት የዴታ ሴንተሩ ድህንነት ይጠብቃሉ።

በዳታ ሰንተሩ አመካኝነት የሚሰጡት አገልግሎቶች በርካታ ሲሆኑ የኢንተርኔት (እና ኢንትራኔት) ግንኙነት ከማሳለጥ እና የክምችት (Storage) አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ የሚከተሉት አገልግሎቶችን ይሰጣል።

1. የቪድዮ ኮንፈረንስ ኣገልግሎት (videoconference Facilities)
ዩኒቨርሲቲው በኣገር ውስጥ እና በውጭ አገር ከሚገኙ ተመሳሳይ የቪድዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት ከተተከለላቸው ጋር ግንኙነት ለማድረግ እና መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚያስችል የቪድዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት ይሰጣል ዳታ ሰንተሩ።

2. ኣይፒ ቴሌፎን ኣገልግሎት (IP Telephony)
በዩኒቨርሲቲው እና ከዩኒቨርሲቲ ውጪ ለሚደረጉ ግንኙነቶች ለማፋጠን ዩኒቨርሲቲው የ500 ኣይፒ ቴሌፎን (IP Telephone) ኣገልግሎት ተዘርግቶ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። የአገልግሎት መስመሩን በተፈለገው ጊዜ መጨመር ይቻላል።

3. የVDI ኣገልግሎት በተመለከተ
ዳታ ሰንተሩ ተማሪዎች (እና ሌሎች) የተሰራው መሰረተ ልማት በመጠቀም የተማከለ ኢንተርኔት፣ ድጅታል ቤተ መፃሕፍት፣ ኢለርኒንግ (E-Learning) እና ሌሎች ኣገልቶች የሚያገኙበት የVDI (Virtual Desktop Infrastructure) ኣገልግሎት ኣጠቃሎ የያዘ ነው። ለዚህ ቴክኖሎጂ ኣገልግሎት የሚውሉ 500 ቲን ክልያንቶች ከነ ሙሉ ኣስፈላጊ መሰረተ ልማት ተተክሎ ያለቀ ሲሆን ሁሉም ተማሪዎች ልዩ መለያ በመጠቀም የሚያስፈልጉ ኣገልግሎቶች ማግኘት ይችላሉ። ይሄንን አገልግሎት በመጠቀም 500 ተማሪዎች በኣንድ ጊዜ ሊያስተናግድ የሚችል የVDI ኮምፒዩተሮች ተከላ ያለቀ ሲሆን ተማሪዎች እየተጠቀሙበት ይገኛሉ።

## 5.7. የ2008 የስራ ዘመን የዘጠኝ ወራት የስራ የኣፈፃፀም ሰንጠረዥ

| ግቦች | ሊሰሩ የታቀዱ ዝርዝር ስራዎች | የስድስት ወራት አፈፃፀም ማብራርያ እና በመቶኛ ሲገለፅ | እቅዱን በመፈፀም ያጋጠሙ ችግሮች ወይም ሁኔታዎች | የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች |
|---|---|---|---|---|
| ግብ 1. የዝግጅት ምእራፍ ስራዎችን በተገቢው በመከወን በድምሩ አስራ አራት ሺ ያህል መደበኛ ተማሪዎችን (5000 አዲስና 9000 ነባር) ለማስተናገድ የሚችል አቅም በመፍጠር የአመቱን ስራ መጀመር | 1.1 የዩኒቨርሲቲው የ2008 እቅድ አሳታፊ በሆነ መልኩ ማዘጋጀት፤ የተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች የየክፍላቸውን እቅድ ያዘጋጃሉ፤ በእቅዶቹ ላይ መግባባት በመፍጠር ወደ ዝርዝር አፈፃፀም መግባት | የዩኒቨርሲቲው የ2008 እቅድ ሃምሌ 2007 ላይ ተዘጋጅቶ በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እንዲዳብር ተደርጎ እና በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ፀድቆ የትግበራው ስራ እየተከናወነ ይገኛል። ከመስከረም 5 እስከ 13 በተደረገው የመምህራንና የሰራተኞች ግምገማዊ ስልጠና ላይም ቀርቦ ውይይትና መግባባት የተደረገበት ሲሆን ለተማሪዎችም ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል። (ኣፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.2 የዝግጅት ስልጠናዎችን ማከናወን (የመምህራን፤ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችና የተማሪዎች የመንግት ፓሊሲዎች፤ ስትራቴጂዎችና አቅጣጫዎች እና ሰላማዊ መማር ማስተማርን በተመለከተ ሰፋፊ ስልጠናዎች ማዘጋጀትና ማስፈፀም)፤ ለመምህራን የሚሰጥ የዝገጅት ስልጠና (Induction Training); የህይወት ክህሎት ስልጠና ለሴት ተማሪዎች መስጠት | በትምህርት ሚኒስቴር ኣስተባባሪነት ለመምህራን፣ ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችና ለተማሪዎች ሰፋፊ ግምገማዊ ስልጠናዎች ተደርገዋል። የመምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ስልጠና ለ7 ተከታታይ ቀና መስከረም መጀመርያ የተደረገ ሲሆን ለነባር ተማሪዎች መስከረም መጨረሻ ለኣምስት ቀናት፣ ለኣዲስ ገቢ ተማሪዎች ደግሞ ጥቅምት መጨረሻ ላይ ለኣራት ቀናት ተሰጥቷል። የስልጠናው ርእሶች (1) የኣንደኛው እትእ ኣፈፃፀምና የሁለተናው እትእ (2) የትምህርት ጥራት ማስጠበቅ ስራችንና የባለድርሻዎች ሚና (3) በተቋማዊ ለውጥ ትግበራ የእስካሁኑ ኣፈፃፀም፣ የኣመራሩ ሚናና ቀጣይ ኣቅጣጫዎች (4) የዩኒቨርሲቲው የ2007 እቅድ ኣፈፃፀምና የ2008 እቅድ ነበሩ። ስልጠናው ጥልቀትና ስፋት የነበረው ሲሆን ማጠቃለያው በተለይ መምህራንና ኣስተዳደር ሰራተኞች ሂስና ግለሂስ በማካሄድ እና ደረጃ (ከA እስከ C)በማስቀመጥ እና መግባባት በመፍጠር የተቋጨ ነበር። ኣዲስ ለተቀጠሩ መምህራን ደግሞ የዝግጅት ስልጠና (Induction Training) በዩኒቨርሲቲው የተሰጠ ሲሆን ለ2200 አዲስ ገቢ ሴት ተማሪዎች ደግሞ በስርኣተ ፆታ ፅ/ቤት ኣስተባባሪነት የህይወት ክፍሎት ስልጠና ተሰጥቷል። (አፈፃፀም 100%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 1.3 ተማሪዎች እርስ በርስ የሚደጋገፉባቸው የአንድ ለአምስት መረቦች (Cooperative Learning Teams) እና የልማት ቡድኖች እንዲደራጁ ማድረግ፤ ቤተመፃህፍቶች ተማረዎች በቡድን እንዲጠቀሙባቸው የሚያስችል አሰራር አጠናክሮ መቀጠል፤ የተማሪዎች የክፍል ተወካዮችን ማስመረጥ | 2356 የተማሪዎች የኣንድ ለኣስት መረቦች (Cooperative Learning Teams) እና 260 የልማት ቡድኖች ተመስርተው ያቀዱዋቸውን ተግባራት በማከናወን ላይ ይገኛሉ። በሁለት ቤተ መፃህፍቶች የኣንድ ለኣምስት ኔትወርክ ኣዳራሾች እንዲኖሩ ተደርገው የ24 ሰኣት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ከነዚህም በተጨማሪ የተማሪዎች መረቦች የመማርያ ክፍሎችን በስፋት ይጠቀማሉ። የክፍል ተወካዮች (በኣንድ ክፍል ሁለት የተማሪ ተወካዮች ሲኖሩ ቢያንስ ኣንዱ ሴት መሆን ኣለባት) ተመርጠው በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሁለት ጊዜ (በየሰሚስተሩ አንድ ጊዜ) ሰፊ የውይይት መድረክ ተዘጋጅቶ ግምገማዊ ውይይት ተደርጎበታል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.4 አምስት ሺ ያህል አዲስ መደበኛ ተማሪዎችን ለመቀበል የሚያስችለን ሰብአዊና ማቴርያላዊ ዝግጅቶችን ማድረግ። የመምህራን ቅጥርና ዝውውር ማከናወን፤ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተጨማሪ ቅጥረ ማካሄድ (የቅጥር መደብ ያልፀደቀላቸው ቦታዎች ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴርና በማስፈቀድ ቅጥሮች እንዲካሄዱ ማድረግ)፤ ግንባታዎች በወቅቱ መጠናቀቃቸው መከታተል፤ ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ግዥዎችና አቅሮቦቶቸ (አልጋ፤ ፍራሽ፤ ጠረጴዛ፤ ወንበር፤ ወዘተ) መሟላታቸውን ማረጋገጥ | በ2008 ወደ ዩኒቨርሲቲያችን የተመደቡ ኣዲስ ተማሪዎች ድምር 5321 ነው (ከተመደቡት ውስጥ የተወሰኑት ያልተመዘገቡ ቢሆንም)። ከዚህ ቁጥር ውስጥ 5244 በቀጥታ በትምህርት ሚኒስቴር የተመደቡልን ሲሆን (የመግቢያ ፈተናውን ወስደው መስፈርቱን ያሚሉ) 32 ሶማልያውያንና 45 ኤርትራውያን (በትምህርተ ሚኒስቴር የተላኩልን) ይገኙበታል። እነዚህን ተማሪዎች ለመቀበል የሚያስችለን የመኖርያ እና የመማርያ ክፍሎች፣ የኣልጋ የፍራሽና የወንበር፣ የመምህራን ቅጥርና ዝውውር፣ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቅጥር ከ2007 መጨረሻ ጀምሮ ዝግጅት ይደረግበት ስለነበር በጥሩ ሁኔታ ተከናውኗል። የሎከሮችና የወንበሮች መዘግየት ኣጋጥሞ የነበረ ቢሆንም ዘግየት ብሎ ይሁን እንጂ ኣቅርቦቱ ተሟልቷል። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 1.5 የግቢ ማስዋብ ስራዎችን ማከናወን [የክረምት ተከላ ማካሄድ፤ በተማሪዎች ካፊቴርያ ፊት ለፊት የሚገኘው ቦታ የማሳመር (landscaping) ስራ መስራት፤ የጣራ ውሃ ለጠቀም | የክረምት ወቅት ተክል ተከላ ሓምሌ 11/2007 ከተከናወነው የተማሪዎች ምረቃ በኣል ጋር በማያያዝ ተከናውኗል። ግቢውን በሳርና በተክሎች የማሳመር (landscaping) ስራ በተመለከተ የዲዛይንና የግንባታ ስራውን በጨረታ ለማከናወን የጨረታ ዶኩመንት በማዘጋጀት ላይ እንገኛለን። | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የሚያስችሉ ስትራክቸሮች (roofwater harvesting structures) መስራት፤ በሁለተኛው ግቢ የችግኝ ማፍያ ጣብያ ማደራጀት] | የክረምት ውሃን ከጣራ ቆርቆሮ ለማጠራቀም የሚያስችሉ ስትራክቸሮችን በራስ ሃይል ለመስራት የተጀመረው ስራ አከባቢው አለታማ በመሆኑ የተጀመረው ቁፋሮ መቀጠል ስላልቻለ በኮንትራክተር ለማሰራት የጨረታ ዶኩመንት መዘጋጀት ይኖርበታል። የችግኝ ጣብያው ግን ተሰርቶ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። (አፈፃፀም 70%) | | |
| | 1.6 የክረምት ተማሪዎችን መቀበልና ማስተናገድ [2007 ክረምት ላይ 4500 ያህል ተማሪዎችን ማስተናገድ፤ ከነዚህ ተማሪዎች አብዛኛዎቹ አዲስ በምንጀምረውና ከክልሉ የቴክኒክና ሞያ ኮሌጆች የተውጣጡና በቴክኖሎጂ የመጀመርያ ዲግሪ የሚማሩ ተማሪዎች ይሆናሉ፤ ከትምህርት ሚኒስቴር ለድህረ ምረቃ ዲፕሎማ ወይም PDGT የሚላኩልን ተማሪዎች ሲሆን ይሄም ዘንድሮ የሚጀመር አዲስ ፕሮግራም ነው። ቀደም ብለው የተጀመሩት የክረምት ትምህርት ፕሮግራሞችም የሚቀጥሉ ይሆናል። ከዚህም ሌላ በክልሉ ምስራቃዊ ዞን እና በዓፋር ክልል አጎራባች ወረዳዎች ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ 300 ጎበዝ ተማሪዎች በሂሳብና ሳይንስ ትምህቶች መሰረት ያደረገው የክረምት አውትሪች ፕሮግራም የሚካሄድ ይሆናል ] | ክረምት 2007 ላይ 4500 ተማሪዎችን ለማስተናገድ አቅሙ የነበረ ቢሆንም በተለያዩ ፕሮግራሞች የተቀበልናቸው (ነባርና አዲስ) ተማሪዎች ድምር 3962 ነው። እንቀበላቸዋለን ብለን ካሰብናቸው ተማሪዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ በትምህርት ሚኒስቴር የሚመደቡልን የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ ተማሪዎች (PGDT) ይሆናሉ የሚል ታሳቢ ተደርጎ የነበረ ቢሆንም በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የተመደቡልን ተማሪዎች ግን ካሰብነው ቁጥር በጣም ያነሰ ነው የሆነው። በሌላ በኩል ደግሞ በትግራይ እና በኣፋር ክልል ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ጎበዝ ተማሪዎች ውስጥ 300 ያህሉን ተቀብለን በሂሳብ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ (STEM Outreach) ለማሰልጠን ኣቅደን የነበረ ሲሆን የተቀበልናቸው ተማሪዎች ግን 90 ሴቶችን ጨምሮ **275** ነበር (ከነዚህ ውስጥ 28 ከዓፋር ክልል የመጡ ሲሆን የተቀሩት 257 ደግሞ ከትግራይ ምስራቃዊ ዞን የመጡ ናቸው)። በኣጠቃላይ የክረምት ተከታታይ ትምህርት እና የSTEM Outreach ፕሮግራም በጥሩ ሁኔታ ተከናውኗል። (ኣፈፃፀም 95%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 1.7 የአመቱን የአካዳሚክ መርሃ ግብር ማውጣትና ማስፀደቅ | የ2008 የአካዳሚክ መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ በሰኔት እንዲፀድቅ ተደርጎ እየተተገበረ ይገኛል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.8 አዲስ ለተመደቡ ተማሪዎች ኦርየንቴሽን መስጠት፤ የዩኒቨርሲቲው የዲሲፕሊን መመርያ ማሰራጨት፤ የትምህርት ክፍል መረጣ ማድረግ | አዲስ ለተመደቡ ተማሪዎች ጥቅምት መጨረሻ ላይ ሰፊ ኦርየንቴሽንና ስልጠና ተሰጥቷል። የተማሪዎች ዲሲፕሊን መመርያ ለተማሪዎች ተሰራጭቷል። የትምህርት ክፍል መረጣ በተገቢው ተከናውኗል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.9 የዩኒቨርሰቲው ሁለተኛው የምረቃ ፕሮግራመ በደመቀ አኳሃን ሃምሌ 2007 ላይ ማከናወን | ሁለተኛው የተማሪዎች ምረቃ በኣል ደማቅ በሆነ ሁኔታ ሓምሌ 11/2007 ተከናውኖ በእለቱ 1027 ተማሪዎች ተመርቀዋል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.10 የተጠናከረ የማባዣ ክፍል በማደራጀት ከነባር ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙትን መፃህፍትና የማስተማርያ ማቴርያሎች ማዘጋጀትና ማቅረብ፡ መፃህፍትን በሶፍት ኮፒ ማሰባሰብ | የተጠናከረ የማባዣ ክፍል በማእከል ላይብረሪ ስር ተደራጅቶ የማባዛት ስራውን እያከናወነ የሚገኝ ቢሆንም የማባዣ ማሽኖች ብልሽት ግን በተደጋጋሚ ያጋጥማል። በተጨማሪም ስራውን በማእከል ከማከናወን ይልቅ በየኮሌጁ እንዲከናወን ስለታመነበት የ12 ማሽኖች (ለያንዳንዱ ኮሌጅ ሁለት) ግዥ ለማከናወን ጨረታ ወጥቶ ትንተናው እየተከናወነ ነው። (አፈፃፀም 85%) | የማባዣ ማሽኖች ተደጋጋሚ ብልሽትና የማባዛቱ ስራ የተማከለ መሆኑ | ተጨማሪ 12 የማባዣ ማሽኖችን በመግዛት በየኮሌጁ የማባዛት ስራ እንዲከናወን ለማድረግ ታስቦ የግዥ ጨረታ እንዲወጣ ተደርጓል |
| ግብ 2. የግንባታ ስራዎች በአግባቡ እየተከናወኑ መሆናቸው መከታተል፣ ያለቁትን ጥቅም ላይ ማዋል፣ አዳዲስ ግንባታዎችን ማከናወን | 2.1 የአምስተኛ ዙር ግንባታዎችን ማከናወንና (በሁለተኛው ግቢ የ33 ብሎኮች) መከታተል፤ ቀደም ብለው መጠናቀቅ የነበረባቸው ግን ያልተጠናቀቁት ግንባታዎች መከታተል፤ በዋናው ግቢ እና በአዲሱ ግቢ የሚከናወኑት የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎችን መከታተል | በሁለተኛው ግቢ ሰኔ 2007 ላይ የተጀመሩት የኣምስተኛ ዙር ግንባታዎች (32 ብሎኮች) ኣፈፃፀም 88.78 ደርሷል። ቀደም ብለው የተጀመሩት የኣራተኛ ዙር 23 ብሎኮች ግንባታቸው ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። በዋናው ግቢ በመከናወን ላይ ያለው የሁለተኛ ዙር መሰረት ልማት ግንባታ አፈፃፀም 95% ደርሷል። የዋናው ግቢ ኣጥር ስራ ደግሞ ተጠናቋል። (ኣፈፃፀም 95%) | | |
| | 2.2 ሁሉን አቀፍ የተማሪዎች የአገልግሎት ማእከል (በዋናው ግቢ) እና የመማርያ ሆስፒታል (በሁለተኛው ግቢ) ዲዛይኖችን | የተማሪዎች ሁለገብ ማእከል (Student Service Center) በዋናው ግቢ ለመገንባት የዲዛይን ስራ በጨረታ ለማሰራት የጨረታ ሰነድ ዝግጅት የተጀመረ ቢሆንም አላለቀም። (አፈፃፀም 30%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ማጠናቀቅ | | | |
| | 2.3 ለሁለተኛው ግቢ ከተመደበው አማካሪ እየተመካከርን ስራዎችን በተገቢው መልኩ እንዲከናወኑ ማድረግ | በሁለተኛው ግቢ በመከናወን ላይ ያሉት የኣምስተኛ ዙር ግንባታዎች በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል። (አፈፃፀም 95%) | የኤሌክትሪክ ወደ ቦታው ኣለመዘርጋት | ከመብራት ሃይል ጋር በመነጋገር እንዲፈታ ተደርጓል |
| | 2.4 የዋናው ግቢ አጥር ስራ መጠናቀቅ፤ በሁለተኛው ግቢ የአጥር ስራ መጀመር፤ በዋናው ግቢ ምእራብ በኩል የሚገኘው መንገድ የኮብልስቶን ስራ ማከናወን፤ | የዋናው ግቢ የኣጥር ስራ በጥሩ ሁኔታ የተጠናቀ ሲሆን በዋናው ግቢ ምእራብ በኩል የኮብልስቶን ስራ በቀሪዎቹ ወራቶች የሚጀመር ይሆናል። የሁለተኛው ግቢ የኣጥር ስራ ወደሚቀጥለው አመት የሚዘዋወር ይሆናል። (ኣፈፃፀም 75%) | | |
| | 2.5 ተጨማሪ አምስት የውሃ ጉድጓዶች ቁፋሮ ማከናወንና የተወሰኑትና ወደ ዩኒቨረሲቲው መስመር መዘርጋት | ኣምስት ተጨማሪ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችን ለማስቆፈር ጨረታ ወጥቶ፣ ኣሸናፊ ተለይቶ፣ ውል ታስሮ ሁለት ጉድጓዶች ተቆፍረው ለጥቅም ተዘጋጅተዋል። ሶስተኛው ጉድጓድ በመቆፈር ላይ ይገኛል። ቀሪዎቹ ሁለቱ ደግሞ የቁፋሮ ቦታዎች በጥናት ስለተለዩ በቀሪው ወራት እንደሚቆፈሩ ይጠበቃል። (አፈፃፀም 80%) | ቁፋሮ በሚካሄዱባቸው ቦታዎች ከካሳ ክፍያና ከቦታ ፈቃድ ጋር ተያይዞ በርካታ ጥያቄዎች ይነሳሉ | ከአከባቢው ኣስተዳደር፣ ከህዝቡ እና ከክልሉ ውሃ ሃብት ቢሮ ጋር ውይይት በማድረግ አብዛኛዎቹን ችግሮት ለመፍታት ተችሏል |
| | 2.6 የማኔጅመንት ህንፃ የዲዛይን፤ የዋናው የዩኒቨርሲቲው መግቢያ በር ዲዛይን ስራ በማጠናቀቅ የግንባታ ስራ መጀመር | በዋናው ግቢ የሚሰራው የማኔጅመንት ህንፃ ዲዛይንና ግንባታ በጨረታ ለማሰራት ጨረታ ወጥቶ አሸናፊው ለመለየት የትንተና ስራ እየተከናወነ ይገኛል። የመግቢያ በር ዲዛይን እና ግንባታ ደግሞ በጨረታ ለማሰራት የጨረታ ዶኩመንት በመዘጋጀት ላይ ይገኛል። (አፈፃፀም 70%) | | |
| | 2.7 በተማሪዎች ምግብ ቤት አዳራሽ ፊት ለፊት የሚገኘው ቦታ ለማስዋብ የላንድስኬፒንግ ዲዛይን እና ግንባታ ስራዎችን ማከናወን | በተጠቀሰው አከባቢ እና በሌሎች የዋናው ግቢ ኣከባቢዎች የላንዲኬፒንግ ዲዛይንና ግንባታ ለማከናወን የሚያስችል የጨረታ ዶኩመንት በዝግጅት ላይ ነው። (አፈፃፀም 30%) | | |
| | 2.8 የተሰራው የስብሰባ አዳራሽ (ኦዲተርየም) ለስብሰባ ምቹ በሆኑ ማቴርያሎች ለሟሟላት የሚያስችል ውል በማሰር ስራውን መከታተል | የስብሰባና የመመረቅያ ኣዳራሹ በተስማሚ ወንበሮችና በኣመቺ የኤልክሮ ሜካኒካል ኣገልግሎቶች ለማሟላት ሁለት ጨረታዎች ወጥተው ኣሸናፊዎች ተለይተው የግንባታ ስራው ተጠናቋል። (ኣፈፃፀም 100%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 2.9 ተጀምረው በማለቅ ላይ ያሉ ዩኒቨርሲቲው የገዛቸው የኮንደሚንየም ቤቶች በማጠናቀቅ ለመምህራን መኖርያ ማስዋል | የመምህራን መኖርያ ኮንደሚንየም ቤቶች ግንባታ ግንቦት 2007 የተጀመረ በአሁኑ ሰአት ግንባታው ተጠናቋል። (አፈፃፀም 95%) | የዲዛይን ማስተካከያዎች ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ተጨማሪ ስራው እስኪፀድቅና ዋጋ እስኪተከልለት የራሱን ጊዜ ወስዷል | ተጨማሪ ስራው የሚጠይቀው ዋጋ በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እንዲፀድቅ ተደርጎ ስራው እንዲቀጥል ተደርጓል |
| | 2.10 በራስ ሃይል (own force) እንዲሰሩ የታቀዱትን የወተትና የከብት ማድለብያ ህንፃዎች፤ የዶሮ ማርቢያ፤ እና ሌሎች ስራዎችን መስራት | በራስ ሃይል የተጀመረው የጀነሬተር ቤት ስራ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። ሁለተኛ ጀነሬተር ተገዝቶ ለገነሬተሩ ማረፊያ ቦታ ተዘጋጅቶለት ጥቅም ላይ ውሏል። የወተትና የከብት ማድለብያ ቤቶች የተጀመሩ ቢሆንም ገና ኣላለቁም። (አፈፃፀም 75%) | | |
| | 2.11 ከተለያዩ የውሃ ጉድጓዶች ወደ ዋናው ሪዘርቫየር የሚመጣውን ውሃ በጊዜያዊነት ማጠራቀም የሚችል ሪዘርቫየር ከግቢው ውጭ መስራት | ከግቢው ውጥ የማጠራቀሚያ ቻምበር (Collection Chamber) በመስራት ወደ ዋናው የውሃ መስመር ያልተያያዙትን ጉድጓዶች ለማያያዝ በተያዘው እቅድ መሰረት ጨረታ ወጥቶ አሸናፊው ተለይቶ ግንባታው በጥሩ ሁኔታ በመከናወን ላይ ይገኛል። (አፈፃፀም 80%) | | |
| | 2.12 ከከተማው አስተዳደር ከከተማው ሆስፒታል ጋር በመተባበር በሆስፒታሉ ውስጥ የህክምና ተማሪዎቻችን የሚጠቀሙበትና ለሆስፒታሉ አገልግሎት የሚውል አንድ ብሎክ መስራት | በከተማው ሆስፒታል የሚገነባው ኣንድ ብሎክ የዲዛይን ማስተካከያ ተደርጎ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊው ተለይቶ የግንባታ ስራው በቅርቡ እንደሚጀመር ይሆናል። (ኣፈፃፀም 70%) | | |
| | 2.13 የዋናው ግቢ ጎርፍ ማውረጃ በኮንክሪት መድፈን፤ ለተማሪዎች መዝናኛ የሚሆን የቴሌቪዥን ቦታ ማሰራት፤ የመኪና ማቆምያ ሼድና ጋራዥ መስራት፤ የጥበቃ ቦታዎችን መስራት፤ | የጎርፍ ማውረጃውን በኮንክሪት ለመድፈን የሚያስችለው ስራ በዩኒቨርሲቲው ስራ ላይ ካሉት ኮንትራክተሮች ለመምረጥ ዝግጅት እየተደረገ ነው። የቴሌቪዥን ማሳያ የሚገነባበት ቦታ ተመርጦ ዲዛይነ ተሰርቶ፣ በጨረታ አሸናፊው ተለይቶ ስራው በጅምር ላይ ነው ያለው። የመኪና ማቆምያ ሼድ ዲዛይን ስራ የተጀመረ ሲሆን ግንባታው ገና አልተጀመረም። የጥበቃ ቦታዎች ስራ ደግሞ የአጥሩ ስራ ስለተጠናቀቀ በቅርቡ ዲዛይኑና ግንባታው የሚጠናቀቅ ይሆናል። (ኣፈፃፀም 70%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ግብ 3. ተቋማዊ መልካም አስተዳደርን ማስፈንና ማስጠበቅ** | 3.1 የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በስፋት የሚያሳትፍ አሰራር መከተል፤ የጋራ መግባባት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ማድረግ | ተማሪዎችን ጨምሮ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ከታች እስከ ላይ የሚያሳትፍ ስርአት ተዘርግቶ በመተግበር ላይ ይገኛል። በእቅዶችና በእቅድ አፈፃፀም ዙርያም አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲታዩና እንዲገመገሙ ይደረጋል። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | 3.2. የተጀመሩት የትምህርት ልማት ሰራዊት ግንባታ ስራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በማድረግ ውጤታማነታቸውን ወደ መለካት መሸጋገር፤ ቀደም ብሎ በተዘጋጀው ማንዋል መሰረተ የመምህራን እና በአስተዳደር ሰራተኞች የአንድ ለአምስት አደረጃጀት እና የልማት ቡድኖች ማጠናከር | በ2008 አንደኛ ሰሚስተር 2356 የተማሪዎች፣ 117 የመምህራን እና 169 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የአንድ ለአምስት መረቦች ተፈጥረዋል። በርከት ያሉ የልማት ቡድኖች (260 የተማሪዎች፣ 41 የመምህራን፣ 24 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች) ደግሞ ተቋቁመው በመስራት ላይ ይገኛሉ። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | 3.3. ሰላማዊ መማር ማስተማር እንዲሰፍን የተማሪዎች አቅርቦቶች (ምግብ፣ መኖርያ፣ ውሃና ፍሳሽ፣ መዝናኛ፣ ወዘተ) በጊዜው እንዲሟሉ ማድረግ። ችግሮች ሲያጋጥሙ አፋጣኝ ምላሾች መስጠት። ተማሪዎችን በሰፊው የሚያሳትፈ አሰራር መከተል። በአካደሚው ዘርፉ በተማሪና በመምህር ዲሞክራያዊ ግንኙነት እንዲሰፍን ማድረግ፤ ትምህርት በወቅቱ መጀመር (First Day First Class)። የጥበቃና የፀጥታ ስርአት ማጠናከር፤ በተማሪዎች መሃከል የእርስ በርስ መግባባት እንዲጎለብት የሰላም ፎረም ማጠናከር። | ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ የአገልግሎት አቅርቦቶች (በተለይም የምግብ የውሃ የመኖርያ እና የህክምና አቅርቦቶች) ሰላማዊ መማር ማስተማር ለማስፈን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው። በዚሁም መሰረት አገልግሎቶቹን ለማሟላት በዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው ጠንካራ ክትትል ይደረግባቸዋል። በየጊዜውም ይገመገማሉ። ከክትትል ስራ ጎን ለጎን ደግሞ ተማሪዎች በነዚህ አቅርቦቶች ዙርያ በካውንስላቸው እና በተለያዩ ክበቦች (ለምሳሌ የፀረ ሙስና ክበብ) አመካኝነት እንዲሳተፉ ይደረጋል። በዩኒቨርሲቲው የተመሰረተው የሰላም ፎረም በተማሪዎች መካከል ሰላማዊ ግንኙነት እንዲኖር የራሱን አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ነው። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 3.4. ከኪራይ ሰብሳቢነት የፀዳ እና በመልካም ስነ ምግባር የታነፀ አመራርና ማህበረሰብ እንዲኖር አስፈላጊው ጥረት ማድረግ፤ | በፌደራል ዋና ኦዲት እና በውስጥ ኦዲት የሚቀርቡ ግኝቶችን መሰረት በማድረግ ማስተካከያዎች ይደረጋሉ። ከሌሎች አካላት (ለምሳሌ በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እና በሲቪል ሰርቪስ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የዩኒቨርሲቲ የስነምግባር መመርያ እንዲኖር ማድረግ፤ ለችግር ተጋላጭ የሆኑትን በማጥናትና በመለየት የክትትል ስራዎችን መስራት፤ ጥርጣሬዎች ሲያጋጥሙ የማጣራት ስራዎች ማካሄድ፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መስጠት፤ ቅሬታዎችን በአግባቡ ማስተናገድ፤ በዋና ኦዲተር እና በውስጥ ኦዲት የሚለዩ ግኝቶችን መሰረት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድ | ሚኒስቴር ባለሞያዎች የቀረቡ) የሚቀርቡ ግኝቶችም እንዲሁ ማስተካከያ ይደረግባቸዋል። የሚቀርቡ ግኝቶችም መጣራት የሚገባቸው ነገሮች ሲያጋጥሙ ኣሳታፊ በሆነ መንገድ እንዲጣሩ ይደረጋል (የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክቶሬትም እየተሳተፈባቸው)። ወደ ህግ መቅረብ ያለባቸው ጉዳዮች ደግሞ በህግ ክፍላችን በኩል ክስ ተመስርቶ ክትትል ይደረግባቸዋል። የዝግጅት ስልጠናዎች ከመምህራንና ሰራተኞች ጋር በተደረገበት ወቅት የመልካም ስነምግባርና ከሙስና የፀዳ ዜጋ ኣስፈላጊነት ግንዛቤ ለማስጨበት ጥረት ተደርጓል። በተጨማሪም በዩኒቨርሲው ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክቶሬት ኣስተባባሪነት ታህሳስ ወር ላይ ከ500 በላይ ተማሪዎች እና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ሃላፊዎች በተገኙበት በዩኒቨርሲቲው ስላለው የመልካም ኣስተዳደር ሁኔታና ያጋጠሙ ችግሮች ኣስመልክቶ ውይይት የተደረገ ሲሆን በኮራፕሽን እና የዜጎች ሚና፣ እንዲሁም ኮራፕሽንን ኣስመልክቶ በአገሪቱ ያለው የህግ ማእቀፍ በማስመልከት የግንዛቤ ማስጨበጫ ፅሁፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል። የመልካም አስተዳደር እቅድም ለብቻው እንዲዘጋጅ ተደርጓል። (ኣፈፃፀም 85%) | | |
| | 3.5. የእቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በየጊዜው ማድረግ። በዚሁም መሰረት የስድስት ወር እና አመታዊ አጠቃላይ ግምገማ ይከናወናል፤ ሰኔት በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ የዲኖችና ዳይሬክተሮች ካውንስል በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ በአስተዳደር ምክትል ፕረዚደንት ፅ/ቤት ስር የሚገኙ ዳይሬክተሮች በየሁለት ሳምንት ይሰበሰባሉ፤ የየሩብ አመቱ ሪፖርቶች ይዘጋጃሉ ለሚለከተወ ክፍል ይላካሉ። | በየደረጃው ያሉ የኣመራር ኣካላት በየጊዜው የክትትል ስብሰባዎችን በተቀመጠው አኳሃን ይካሄዳል። የስድስት ወር ኣጠቃላይ ግምገማ የካቲት 25/2008 ላይ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ ሰብሳቢ በተገኙበትና መምህራንና ሰራተኞች በተገኙበት ተከናውኗል። የየሩብ ኣመቱ ሪፖርቶች ከየክፍሉ እንዲቀርቡ ይደረጋል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | 3.6. የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እና የልምድ | በርካታ የልምድ ልውውጦችና ስልጠናዎች ተከናውነዋል። (አፈፃፀም 75%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ልውውጦችን ማከናወን | | | |
| | 3.7. የዩኒቨርሲቲ ስትራቴጂክ ፕላን መሰረት በማድረግ የካስኬዲንግ ስራዎችን መስራት | የዩኒቨርሲቲው አዲስ ስትራቴክ እቅድ (ከ2008 – 2012) በባላንስድ ስኮር ካርድ (BSC) መሰረት ተዘጋጅቶ በየደረጃው ውይይት ተደርጎበት እንዲዳብር ከተደረገ በኋላ በቦርድም ውይይት ተደርጎበት እንዲፀድቅ ተደርጎ ለሁሉም የዩኒቨርስቲው አካላት ለትግበራ ተበትኗል። የካስኬዲንግ ስራዎች ግን አልተጠናቀቁም (አፈፃፀም 75%) | | |
| | 3.8. የካይዘን ስራዎችን ማጠናከርና መተግበር | በተመረጡ የዩኒቨርስቲው ክፍሎች (የንብረት ክፍል ስቶር፣ የተማሪዎች ምግብ ቤት እና ላቦራቶሪዎችና ዎርክሾፖች) የካይዘን ትግበራዎች ተከናውነዋል። በዘርፉ እውቀት ያላቸው ባለሞያዎችን በማምጣት የካይዘን ስልጠና በየደረጃው ለሚገኙ የዩኒቨርሲቲ ሃላፊዎችና ሰራተኞች የተሰጠ ሲሆን ስልጠናው በተግባራዊ ስራዎች የተደገፈ ስለነበረ ውጤታማ ነበር። (አፈፃፀም 80%) | | |
| | 3.9. ለተማሪዎች ካውንስል፤ ለተማሪ ክበቦች፤ ለመምህራን ማህበር፤ ለቁጠባና ብድረ ማህበር፤ እና ለሌሎች አደረጃጀቶች ድጋፍ ማድረግ | በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ላሉት የተለያዩ አደረጃጀቶችና ክበቦች ድጋፍ ይደረጋል። (አፈፃፀም 80%) | | |
| | 3.10. ህጉን የተከተለና የተቀላጠፈ የግዥና ፋይናንስ ስርአት እንዲኖር ማድረግ፤ ዋና ዋና የግዥ ስራዎችን በታቀደ መልኩ እንዲከናወኑ ማድረግ፤ የንብረት አያያዝና ሪፖርቲንግ ስርአት ማሻሻልና ማጠናከር | የግዥና የክፍያ ሂደቱ ህግን የተከተለ ለማድረግ የሚሰራው ስራ ጥሩ ቢሆንም በቅልጥፍና በኩል የሚፈለገውን ያህል አይደለም። (አፈፃፀም 80%) | በአቅራቢዎች በኩል የዶላር አቅርቦት ስላጠረ ኤልሲ ለመክፈት ተቸግረናል የሚሉ ተደጋጋሚ እሮሮዎች ይቀርባሉ። ከስፔሲፊኬሽን ውጭ ወይም ጥራታቸውን ያልጠበቁ እቃዎችን ለማቅረብ የሚደረጉ ሙከራዎችም የሚፈጥሩት ፈተና ቀላል አይደለም። የጨረታ ትንተና ከሚፈለገው በላይ ጊዜ ይወስዳል። | የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር የሚያካትተው የአስተዳደር ካውንስል የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ጉዳዮችን በማየት ውሳኔዎችን ያሳልፋል፣ ጠንካራ ክትትልም ይደረጋል። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3.11. የወፍጮ ስራና የዳቦ መጋገር ስራ በግቢው ውስጥ ማከናወን | የወፍጮና የዳቦ መጋገር ስራ በግቢው ውስጥ ለማከናወን መሳርያዎች የተተከሉ ቢሆንም ይሄንን ስራ የሚያከናውኑ ባለሞያዎች በኮንትራት ስራ (Outsource) ለማሰራት የተደረገው ሙከራ ግን ውጤታማ ሊሆን ኣልቻለም (በሚቀርብ ዋጋ ውድነት ወይም በተጫራቾች እጥረት)። ስራውን በውድድር የማሰራት ጥረቱ (ለምሳሌ በጨረታ) የሚቀጥል ይሆናል። | | |
| | 3.12. ለተማሪዎች የሚቀርብ ዳቦ ዩኒቨርሲቲው በገዛቸው የዳቦ መጋገርያ ማሽኖች በከፊልም ቢሆን እንዲቀርብ ማድረግ። ሰራተኞቹን በተመለከተ ወደ ውጭ ወጥቶ (outsource ተደርጎ) እንዲሰራ ይደረጋል | ስራውን ወደውጭ ለማውጣት (Outsource ለማድረግ) ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም ከላይ እንደተቀመጠው ሊሳካ አልቻለም፤ ስለዚህ ዳቦ በጨረታ እየተገዛ እየቀረበ ይገኛል። | | |
| | 3.13. አዲስ አበባ የሊያይዘን ፅ/ቤት ስራ ማስጀመር | ሊያይዘን ፅ/ቤቱ ስራ ጀምሯል፣ አስተባባሪ ተመድቦለት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። በሰው ሃይል እና በማቴርያል የማጠናከሩ ስራ ግን የሚቀጥል ይሆናል። (አፈፃፀም 80%) | | |
| | 3.14. አዲስ እና የተሻሻለ የስራ መዋቅረ በማዘጋጀት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ እንዲያፀድቀው ተደርጎ ወደ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በማስፀደቅ በ2008 እንዲተገበር ማድረግ | የተዘጋጀው ረቂቅ መዋቅር ኣስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎለት እና ዝርዝር የስራ ስፔሲፊኬሽን ተዘጋጅቶለት በሚቀጥለው የቦርድ ስብሰባ የሚቀርብ ሲሆን ከፀደቀ በኋላ ወደ ሲቪል ሰርቪስ የሚላክ ይሆናል። (60%) | | |
| | 3.15. በመኪና እጥረት ምክንያት የሚያጋጥመውን የትራንስፖርት አገልግሎት ችግር ለመቀነስ የሰርቪስ መኪኖችን መከራየት፤ የቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ እንዲቋቋም በማድረግ ከሚገዛቸው መኪኖች ዩኒቨረሲቲው እንዲከራይ ማድረግ | የሰርቪስ መኪና እጥረት ለማቃለል ተጨማሪ ኣውቶቡሶች የተላኩልን ሲሆን ከዚሁም ጎን ለጎን ተጨማሪ ሁለት ኣውቶቡሶችን በመከራየት ጥሩ የሰርቪስ ኣገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል። ከሰርቪስ መኪኖች ጋር ተያይዞ ያለው ችግር ባለው ደምወዝ በቂ ቁጥር ያላቸው ሾፌሮችን ማግኘት ኣለመቻል ነው። (ኣፈፃፀም 95%) | የተፈለገው የሾፌሮች ቁጥር ማግኘት ኣለመቻል | ዩኒቨርሲቲው ከሰራተኞቹ ውስጥ ለሾፌርነት መሰልጠን የሚፈልጉትን በመለየት የሚያሰለጥን ሲሆን ለሾፌርነት የሚፈለገው ደረጃም ዝቅ እንዲልለት ለሲቪል ሰርቪስ ጠይቆ ተፈቅዶለታል። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3.16. በቀልጣፋ ለውጥ አምጪ መሳርያ (quick wins) መሰራት ያለባቸውን በመለየት እንዲከናወኑ ማድረግ | በቀልጣፋ ለውጥ አምጪ መሳርያ መሰራት ያለባቸው ስራዎች ተለይተው ተተግብረዋል። በዚህ ረገድ ወደ ታች መውረድ ያለባቸው ስራዎች (ለምሳሌ የመምህራን ቅጥር) በማውረድ ቅልጥፍና ለመጨመር ተችሏል። (አፈፃፀም 75%) | | |
| | 3.17. ስራዎችን ወደ ታች ማውረድ፤ ከሌክቸረር በታች ያሉት የቅጥርና የእድገት ስራዎች ሙሉ ለሙሉ ኮሌጅ ላይ እንዲያልቁ ማድረግ፤ | በእቅዱ መሰረት የቅጥር እና የእድገት ስራዎች ወደ ታች (ማለትም ኮሌጅና ትምህርት ክፍል) እንዲወርዱ ተደርጎ እየተሰራበት ይገኛል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 3.18. የተገልጋዮች እርካታ ጥናት ማከናወን | የተገልጋዮች እርካታ ጥናት በሶስት ተከፍሎ (ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ድፋፍ ሰጪ ሰራተኞች) ተካሂዶ ውጤቱ እንዲሰላ ተደርጓል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| ግብ 4. የመምህራን ልማት ማጠናከር | 4.1 መምህራንን ለሁለተኛ እና ለሶሥተኛ ዲግሪ ትምህርት መላክ | 296 ያህል የዩኒቨርሲቲው መምህራን የትምህርት ደረጃቸውን ለማሳደግ በትምህርት ላይ ይገኛሉ። ከዚህ ቁጥር ውስጥ 229 የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጥናት የሚገኙ ሲሆን የተቀሩት 66 ደግሞ ለዶክትሬት ዲግሪ እና ለስፔሻላይዜሽን በመማር ላይ ይገኛሉ። ትምህርት ላይ ካሉት ውስጥ 273 አገር ውስጥ እየተማሩ ሲሆን 23 ደግሞ ውጭ አገር በማጥናት ላይ ይገኛሉ (አፈፃፀም 95%) | | |
| | 4.2 በትምህርት የሚገኙ መምህራን የትምህርት ሁኔታቸወ መከታተል | በየኮሌጁ እና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ክትትል ይደረግላቸዋል። ተገቢውን በማያሟሉት ላይ እርምጃ ይወሰዳል [ለምሳሌ ደምወዝ አለመክፈል፣ እና ትምህርታቸውን ጨርሰው በማይመለሱ ላይ በውላቸው መሰረት ክስ ይመሰረትባቸዋል] (አፈፃፀም 95%) | | |
| | 4.3 መምህራን የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም (HDP) እንዲከታተሉ ማድረግ | የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም (HDP) በ2007 ተጀመረ ያኔ ይማሪ ከነበሩት አብዛኛዎቹ ስልጠናውን ያጠናቀቁ ሲሆን በ2008 ደግሞ በሁለት ሴክሽኖች ተከፋፍለው 56 መምህራን እየሰለጠኑ ይገኛሉ። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 4.4 በፔዳጎጂ እና ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች እንዲሰጥ ማድረገ (በተለይ ለአዳዲስ መምህራን) | ስልጠናው በዩኒቨርሲቲው ባለሞያዎች ተሰጥቷል። (100%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 4.5 የውጭ አገር መምህራንን ቅጥር ማካሄድ (ከህንድ፤ ከፊሊፒንስ እና ከሌሎች አገሮች) | ከህንድና አገር የቅጥር ስራ ተከናውኗል። ሆኖም ከተመረጡት 20 ያህል መምህራን ወደ ስራ የመጡት 12 ብቻ ናቸው። (አፈፃፀም 70%) | | |
